ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 042 ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# የቴክኒክና ሙያ ዘርፉን ለማሳደግ ከቻይና-አፍሪካ አቻ ተቋም ጋር የልምድ ልውውጥ ተደረገ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍን ለማሳደግ ከቻይና-አፍሪካ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኅብረት ጋር የልምድ ለውውጥ ተደረገ። በሀገራት መካከል የቴክኖሎጂ፣ የእውቀትና የልምድ ሽግግር ማድረግ ወሳኝ መሆኑ ተጠቁሟል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የቻይና-አፍሪካ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኅብረት በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የልምድ ልውውጥና የውይይት መድረክ ትናንት ተካሄዷል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር) በዕለቱ እንደተናገሩት፣ ከዲጂታላይዜሽን ጋር ተያይዞ ወጣቶች የሚፈልጓቸው ዓይነት ሥልጠናዎችን ለመስጠት በቴክኖሎጂ ከበለጸጉ ሀገሮች ጋር በትብብር መሥራት ለዘርፉ ማደግ ወሳኝ ሚና አለው።

ከሀገራት ጋር የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ገጽታ በመቀየር ብዙ ወጣቶችም ቴክኒክና ሙያ መግባት እንዲችሉ የሚረዳ ነው ብለዋል።



ተሻለ በሬቻ(ዶ/ር)



ፕሮፌሰር ሻንዡ

እንደ ዶክተር ተሻለ ገለጻ፣ ትስስሩ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጎን ለጎን የሥራ እድል ለመፍጠር እንዲሁም የገበያ ልማት ለማሳደግ ያግዛል።

በሁለቱ ሀገራት መካከል የተጀመረው የልምድ ልውውጥ ሙያ ነክ የሆኑ ትምህርቶችን ለማስፋፋት የሚደግፍ መሆኑንም ነው ዶክተር ተሻለ የገለጹት።

ፍላጎት መር የሆነ ሥልጠና ለመስጠት በቂ ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ተሻለ፣ ከቻይና ቴክኒክና ሙያ ኅብረት ጋር የተደረገው ትስስር ውስንነቱን እንደሚቀርፍ ጠቁመዋል።

የቴክኒክና ሙያ ዘርፉን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በአማራ ክልል ተጥሎ በነበረው የሰዓት እላፊ ላይ ማሻሻያ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል አንጻራዊ ሰላም መምጣቱን ተከትሎ ተጥሎ በነበረው የሰዓት እላፊ ገደብ ላይ ማሻሻያ መደረጉን ኮማንድ ፖስቱ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ እና የኮማንድ ፖስቱ አባል መንገሻ ፈንታው( ዶ/ር) በክልሉ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ በኮማንድ ፖስት የሰዓት እላፊ ተጥሎ እንደነበር

በአማራ ክልል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# አደጋ የደቀነው የሐሰተኛ መረጃዎች ስርጭት

**ተስፋ ፈሩ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መደበኛ የብዙኃን መገናኛዎችን ጨምሮ በማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩ ሐሰተኛ መረጃዎች እየተበራከቱ መጥተዋል። የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያስችላል የተባለ አዋጅ ጸድቆ ሥራ ላይ ከዋለ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ቢቆጠርም ችግሩ በመቀነስ ፈንታ እየሰፋ ይገኛል። ለመሆኑ የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት እየጨመረ የመጣው ለምንድን ነው? በሀገር ላይ የደቀነውን አደጋ ለመቀልበስ ምን መደረግ አለበት?

አንተነህ ፀጋዬ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነት ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መምህርና



ተመራማሪ ናቸው። ሐሰተኛ መረጃዎች በተለይ ከለውጡ ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመሩ መሄዳቸውን

አደጋ የደቀነው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል













# ቱሪዝም በሳይንስ ሙዚየም

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪዝም ሀብት ያላት ሀገር ብትሆንም እስካሁን ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ያህል ጥቅም እያገኘች አይደለም። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል በሀገሪቱ ስላሉት የቱሪዝም መዳረሻዎች ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጪ ጎብኚዎች በቂ መረጃ አለመኖሩ እንደ አንድ ምክንያት ይጠቀሳል።

የቱሪዝም ሚኒስቴርም በአዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየም ሀገር አቀፍ የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደ ርዕይ እያካሄደ ይገኛል። በዓውደ ርዕዩ የተሳተፉ የዘርፉ ባለ ድርሻ አካላትና ጎብኚዎች የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ እድገትን ለማስቀጠል የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ተናግረዋል።

የባሕልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማኅበር አባል የሆነው ጋዜጠኛ ሰለሞን ግርማ እንደሚለው፤ በዘርፉ ከተሰማሩ ጋዜጠኞች በሀገሪቱ ያሉትን የቱሪስት መዳረሻዎች ለሌሎች ለማስተዋወቅ በሚያስችል ደረጃ በቂ እውቀት ያላቸው ጥቂቶች ናቸው። ሁሉንም የቱሪስት መዳረሻዎች በአካል እየተገኙ ለመዘገብ ደግሞ ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ይጠይቃል። የቱሪዝም ዓውደ ርዕይ መዘጋጀት በአንድ ቦታ በሀገሪቱ ስላሉት አብዛኛዎቹ የቱሪዝም መዳረሻዎች መረጃ ለማስጨበጥ የሚያስችል ይሆናል።

በዚህ መልኩ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የሚቀርቡ ትዕይንቶች ለጎብኚዎች ብቻ ሳይሆን በዘርፉ ለተሠማሩ ባለ ድርሻ አካላትም ግንዛቤ የሚያስጨብጥና የልምድ ልውውጥ እንዲኖር በር የሚከፍት ነው። በመሆኑም እንዲህ አይነት ዓውደ ርዕዮች እንደ ሀገር በተለያዩ ቦታዎችም መዘጋጀት ያለባቸው ሲሆንም ክልሎችም በሥራቸው ያሉትን የቱሪስት መዳረሻዎች ለማስተዋወቅ ተመሳሳይ ዝግጅቶችን ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው ተናግሯል።


የሆቴል ማናጀር የሆነችው ወይዘሪት ዮስቴና አስቻለው




ጋዜጠኛ ሰለሞን ግርማ



ወይዘሪት ዮስቴና አስቻለው



አቶ አሕመድ መሐመድ



አቶ ይበልጣል አሰፋ

ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

በበኩሏ እንደምትናገረው በሀገሪቱ ያለው የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም የሚጠበቀውን ያህል ጥቅም እያስገኘ አይደለም። ዘርፉ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉበት ቢሆንም አሁን የተፈጠረውን አቅም ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም ጠንካራ የማስታወቂያ ሥራ መሥራት የሚጠበቅ ይሆናል። የማስታወቂያ ሥራዎቹም መሠራት ያለባቸው በተቀናጀ መልኩ እንደ ሀገር ያለውን የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ እንቅስቃሴ በሚያሳይ መልኩ ሊሆን ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ደረጃቸውን የጠበቁ በርካታ ሆቴሎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል። በቡራዩ ሎጅ እየተገነባ ያለው ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የአፍሪካን አመጋገብ አለባበስና ሌሎች ባሕሎች የሚያንጸባርቁ ሀምሳ አራት ክፍሎች ተዘጋጅተዋል። እነዚህንና መሰል የዘርፉን ለውጦች ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለቀሪው ዓለምም ማስተዋወቅ ይጠበቃል። ለዚህም በአሁኑ ወቅት በቱሪዝም ሚኒስቴር አዘጋጅነት እየተካሄደ ያለው ዓውደ ርዕይ አይነት በአፍሪካና በሌሎ አህጉራትም የሚካሄድበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል።

«በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያወዳድሩን የሚችሉ ተፈጥሯዊ መስህቦች ቢኖሩንም በሚጠበቀው ደረጃ አልተዋወቁም» ያሉን ደግሞ በአፋር ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አሕመድ መሐመድ ናቸው።

የአፋር ክልል በዓለም ካሉት የማያቋርጡ ስድስት እሳተ ገሞራዎች መካከል አንዱ የሆነውን ኤርታሌንና ዝቅተኛ ቦታ የሚባለውን ዳሉልን የያዘ ነው። በተጨማሪም በርካታ ተፈጥሯዊና ባሕላዊ መስህቦችም አሉት። ነገር ግን በሀገር ውስጥም ሆነ በቀሪው ዓለም በሚጠበቀው ደረጃ የማይታወቅ በመሆኑ በክልሉ ያለው የቱሪዝም እንቅስቃሴ የተገደበ ነው። በመሆኑም በዘርፉ የሚሠሩት የልማት ሥራዎች መጠናከር እንዳለባቸው ሁሉ የማስተዋወቁም ሥራ ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ዓውደ ርዕዩ በቀላሉ ልናሳካው የማንችለውን እድል በነፃ የሚሰጠን ነው ያሉን ደግሞ ዓውደ ርዕዩን ሲጎበኙ ያገኘናቸው አቶ ይበልጣል አሰፋ ናቸው። አቶ ይበልጣል እንደሚያብራሩት በኢትዮጵያ በርካታ የቱሪዝም መዳረሻዎች ቢኖሩም ከአቅም አኳያ ሁሉንም ለመጎብኘት ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አስቸጋሪ ነው። የውጪ ጎብኚዎችም ቢሆኑ ሁሉንም ቦታዎች በአካል በመገኘት ሊያዩ የሚችሉበት አጋጣሚ አይኖርም። እንደዚህ አይነት ዓውደ ርዕዮች ግን ስለሁሉም ግንዛቤ ከመስጠት ባለፈ በአካል ማየት ለሚፈልግም ከመሄድ በፊት በቂ መረጃ የሚያስጨብጡ ናቸው።

በተጨማሪ ዓውደ ርዕዩ በዘርፉ ለተሠማሩ ባለሙያዎችና የመንግሥት አካላት በቱሪስት መዳረሻነት ሊለሙ የሚችሉ ቦታዎችን ለመለየትና ለማልማት ልምድ ለመውሰድም ይጠቅማል። በመሆኑም እንዲህ አይነት ዓውደ ርዕዮችን ለአንድ ግዜ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ቦታዎች በማካሄድ ዘርፉን የበለጠ ማስተዋወቅ ይጠበቃል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

# አሽከርካሪዎች በሕግ በተደነገገው የክብደት መጠን እንዲጭኑ አስተዳደሩ አሳሰበ

**በኃይሉ አበራ**

ሞጆ፡- እያንዳንዱ የተሽከርካሪ ባለቤትና አሽከርካሪዎች በባለቤትነት ስሜት በሕግ በተደነገገው የክብደት መጠን መሠረት እንዲጭኑ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አሳሰበ።

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሞጆ ክብደት እና መጠን መቆጣጠሪያ ጣቢያ ኃላፊ በሞጆ ከተማ ሰሞኑን በተደረገው የግንዛቤ ማስጨበጫ ጉብኝት ላይ አሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በሕግ በተፈቀደላቸው ክብደት መጠን በመጫን ንብረታቸውን፣ መንገድ እና ድልድዮችን ከብልሽት መታደግ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

በቀን ከ400 በላይ ተሽከርካሪዎችን የመመዘን አቅም የነበረውና በጃፓን መንግሥት የተገጠመው የሞጆ የተሽከርካሪ ሚዛን ጣቢያ በኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን መዋዠቅ ምክንያት በመበላሸቱ በቀን ከ80 እስከ 120 ተሽከርካሪ ብቻ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አመላክተዋል።

በጃፓን መንግሥት ድጋፍ በሀገሪቱ 14 አካባቢዎች በተመሳሳይ ጊዜ የተገጠመ ቢሆንም በብልሽት ምክንያት አምስቱ ብቻ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ጠቁመው፤ ይሁንና በቀጣይም ጥር ወር አካባቢ ሙሉ ጥገና ተደርጎለት ወደ አገልግሎት ይመለሳል ብለዋል።

በማንኛውም የኢትዮጵያ መንገዶች ጠቅላላ ክብደታቸው ከሶስት ሺህ 500 ኪሎ ግራም በላይ በሆኑ ተሽከርካሪዎች፣ የተጣመሩ ተሽከርካሪዎች እና ተሳቢዎች ከክብደት በላይ መጫንን ለመከልከል ለወጣው ሕግ ተገዢ መሆን አለባቸው ብለዋል።

ነገር ግን በእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች፣ የተፈጥሮ አደጋ መከላከል ሥራ ላይ በተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፣ በድንገተኛ አደጋ የወደሙ መሠረተ-ልማቶችን በመገንባት ሥራ ላይ በተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፣ ኢትዮጵያ በተፈራረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መነሻነት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች፣ የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት አካባቢ የሚንቀሳቀሱ የግንባታ ተሽከርካሪዎች እና በልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች በሕጉ አይገደዱም ብለዋል።

በጣቢያዎች የሚደረገው ቁጥጥር እና ቅጣት ዘላቂ መፍትሔ የማያመጣ በመሆኑ የተሽከርካሪ ባለቤቶች እና አሽከርካሪዎች በባለቤትነት ስሜት በሕግ በተፈቀደው ክብደት ብቻ እንዲጭኑ አሳስበዋል።

መንግሥት ለክብደት ገደብ ሲያስቀምጥ ከገደቡ በላይ መጫን በመንገድ ሀብት ላይ የሚያደርሰውን ከፍተኛ ጉዳት ከግምት በማስገባት ስለሆነ ሁሉም አሽከርካሪና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ሕጉን በማክበር ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚገባቸውም ተመላክቷል።

የተሽከርካሪዎችን ክብደት መቆጣጠር ዋና ዓላማ በመንገዶች ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው የአክስል ክብደት መጠን በላይ ጭነት ጭነው በከፍተኛ ወጪ የተገነቡ የመንገድ አውታሮች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመከላከል እንዲሁም መንገዶች እና ድልድዮች ሳይበላሹ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

ከተፈቀደው ክብደት በላይ ጭነው መንገዶችንና ድልድዮችን ስለሚጎዱ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በመላ ሀገሪቱ ቁጥራቸው 14 የሚደርሱ የሚዛን ጣቢያዎች አቋቁሟል። እነዚህም በሞጆ፣ ሆለታ፣ ሱሉልታ፣ ሠንዳፋ፣ ዲማ(ሰበታ)፣ ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ አዋሽ፣ ሠመራ፣ ደንገጎ፣ ኮምቦልቻ፣ ጢቅ(ደጀን)፣ ወረታ፣ የሓ (መቀሌ) አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ ሲሉም ኃላፊው ጠቁመዋል።

የወንጀል መከላከል ድልድል ኢንስፔክተር ምስጋና ያደታ በበኩላቸው፤ ሚዛን ጥሰው የሚሄዱ መኪናዎች ሲያጋጥሙ መኪና ሲያመልጣቸው ድጋፍ በመስጠት በኩል ከሞጆ የሚዛን ጣቢያ ጋር ከሚሠሩ ባለድርሻ አካላት በጋራ የሕግ ማስከበር ሥራ የሚሠራ መሆኑን ገልፀዋል። ኅብረተሰቡ የተቋሙ ባለድርሻ አካላት እና ብዙኃን መገናኛዎች መንገዶችን ከጉዳት ከመከላከል አንጻር የማይናቅ ሚና ያላቸው በመሆኑ ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የኢትዮጵያ መንገድ አስተዳደር ጥሪ አቅርቧል።

የከባድ ጭነት አሽከርካሪዎችም መጫን ከሚገባቸው ክብደት በላይ የሚጭኑ ከሆነ ንብረቱ ስለሚበላሽ ንብረቱም እንዲቆይና ተፈላጊውን ያህል አገልግሎት እንዲሰጥ መክረዋል። የተሽከርካሪው ባለንብረትም የሕግ የበላይነትን በማክበር ንብረታቸውን መጠበቅ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ከመንገድ ትራንስፖርት ኤጀንሲ አቶ ካሳሁን ደበበ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ከሞጆ ከተማ ክብደት መቆጣጠሪያ ጣቢያ ጋር በመሆን በተሠሩ የቅንጅት ሥራዎች መመዘኑን የማረጋገጥ ሥራዎችን እየሠራ ነው።

ሞጆ ከተማ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ስላሉና በርካታ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች የሚተላለፉባት ከተማ መሆኗን አስታውሰው በከተማዋ በተለያዩ መግቢያ አማራጭ መንገዶች ስላሉ በቅንጅት ቁጥጥር እየተደረገ ነው ብለዋል።



# በክልሉ አንድ ሺህ ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት ዝግጅት እየተደረገ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል በዘንድሮው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አንድ ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት እየተሠራ እንደሚገኝ የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ።

የክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡጁሉ ሉአል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 የምርት ዘመን በበጋ መስኖ ስንዴ አንድ ሺህ ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል ።

በአሁን ወቅት በዝግጅት ምዕራፍ ላይ እንደሚገኙ የተናገሩት ኃላፊው እስካሁን ድረስ 11 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ገልጸዋል።

በዘር ከሚሸፈነው አንድ ሺህ ሄክታር መሬት ከ30 ሺህ በላይ ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን በመግለጽ፤ በአንድ ሄክታር መሬት ከ25 እስከ 30 ኩንታል ምርት ለመግኘት እቅድ ተይዟል ብለዋል።

አቶ ኡጁሉ እንደገለጹት፤ ባለፈው ዓመት የሙከራ ጊዜ በመሆኑ በሁለት የግብርና ሥነምሕዳር አከባቢዎች የበጋ መስኖ ስንዴ የማልማት ሥራ ተሠርቷል።

በዚህም ሙከራው የተደረገው ማጃንግ ዞን ወይና ደጋ አካባቢና በአኙዋክ ዞን ቆላማ አካባቢ የበጋ መስኖ ስንዴ እንደተዘራ አስረድተዋል።

በተሠራው ሥራ ወይና ደጋ አካባቢ በጣም ውጤታማ መሆን የተቻለ ሲሆን በቆላማ አካባቢ ለአካባቢው የሚሆን የስንዴ ዘር መጠቀም ባለመቻሉ ውጤታማ መሆን እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት በወይና ደጋ አካባቢ የማስፋት ሥራ እየተሠራ ሲሆን፤ በቆላማ አካባቢ ውጤታማነትን ለማምጣት ከአካባቢው ሥነምሕዳር ጋር የሚሄድ የስንዴ ዝርያ የማጥናት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ኃላፊው እንደተናገሩት የዘንድሮ ዓመት የበጋ መስኖ ስንዴን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ በአመራሩ የተደገፈ ግብረ ኃይል የማቋቋም ሥራ የሚሠራ ሲሆን፤ ባለሙያውን በማደራጀት የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት የግብርና ቢሮው እየሠራ እንደሆነ አስረድተዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ሥራ አዲስ እንደመሆኑ ለአርሶ አደሩ የምክር አገልግሎት የመስጠትና አርሶ አደሩን በማደራጀት በኩታ ገጠም እርሻ እንዲሠራ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አክለው ገልጸዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተደረገ ያለውን ተግባር የመደገፍ ሚናው የጎላ ነው ያሉት አቶ ኡጁሉ፤ ገበሬው ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ ዓመቱን ሙሉ እንዲያመርት እድል ፈጥሯል ብለዋል።

ከአንዳንድ አካባቢዎች የሥነ-ምሕዳር ሁኔታ አንጻር ሰብሎች ሲደርሱ በዝናብ የመጎዳት ሁኔታ ስለሚኖር ይህን ለመከላከልም ይረዳል ሲሉ አክለው ገልጸዋል።

በመጨረሻም ኃላፊው የልማት ድርጅቶች በሚያስቀምጡት መንገድ የክልሉን የግብርና ሃብት በአመራሩ በመደገፍ ውጤታማ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።



አቶ አሸናፊ ክንፉ

# በክልሉ 11 ሺ 927 ሄክታር መሬት በሩዝ ምርት መሸፈኑ ተገለጸ

ፍሬሕይወት አወቀ

አዲስ አበባ፤- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል 11 ሺ 927 ሄክታር መሬት በሩዝ ምርት የተሸፈነ መሆኑን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ክንፉ ገለጹ።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የሩዝ ምርት በአዲስ መልክ ታቅዶ በስፋት እየተሠራበት ነው ብለዋል። በመሆኑም በክልሉ በመኸር ወቅት ብቻ 11 ሺ 927 ሄክታር መሬት በሩዝ ምርት የተሸፈነ ሲሆን፤ ክልሉ ለሩዝ ምርት ከፍተኛ አቅም ያለው መሆኑንም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ ቀደም በአካባቢው በመኸር ወቅት ይመረት ከነበረው የሩዝ ምርት መጠን በአሁን ወቅት ከሦስት እጥፍ በላይ ማሳደግ ተችሏል። በክልሉ ከዚህ ቀደም ከሦስት ሺ እስከ አራት ሺ ሄክታር መሬት ብቻ በሩዝ ምርት የሚሸፈን መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን ላይ በመኸር ወቅት ብቻ 11 ሺ 927 ሄክታር መሬት በሩዝ ምርት መሸፈን እንደተቻለ ገልጸዋል። ይህም ክልሉ በክረምት የግብርና ሥራው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበበት ሥራ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

የሩዝ ምርት በክልሉ ከዚህ ቀደም በመኸር ወቅት በስፋት ተመርቶ አይታወቅም ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አሁን ላይ ከሦስት እጥፍ በላይ የማሳ ስፋት ላይ ማምረት መቻሉን ገልጸዋል። እንደሳቸው ገለጻ ክልሉ በሩዝ ልማት ዘርፍ ሰፊ ሥራ መሥራት የሚቻልበት ምቹ ሁኔታና ሰፊ ዕድል አለ።

የሩዝ ምርት የመድረሻ ጊዜው እንደዝርያው የሚለያይ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል የቢሮ ኃላፊው፤ ከሦስት እስከ አራት ወራት ጊዜ እንዲሁም ከአራት እስከ አምስት ወራት ጊዜ የሚወስዱ የሩዝ ዝርያዎች ስለመኖራቸው ተናግረዋል። ከሐምሌ ጀምሮ የተዘራው የሩዝ ዘርም በቀጣይ ኅዳር ወር አካባቢ ለአጨዳ የሚደርስ መሆኑን አመላክተዋል።

ክልሉ በሩዝ ምርት ላይ በስፋት ለመንቀሳቀስ በዕቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ ከዚህ ቀደም በሁለት የምርት ወቅቶች ማለትም በበልግና በመኸር ወቅት ከ15 ሺ ሄክታር የበለጠ የሚመረት እንዳልነበር ተናግረዋል። ይሁንና በአሁን ወቅት ለሩዝ ምርት በተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የምርት መጠኑን በእጥፍ ማሳደግ ተችሏል ነው ያሉት።

እሳቸው እንዳሉት አካባቢው ዕምቅ አቅም ያለው በመሆኑ በስፋት ሊሠራበት እንደሚገባና በሀገሪቱ የሚታየውን ገበያ በማረጋጋት በኩል ትልቅ አስተዋፅዖ አለው።

ሩዝ አሁን ባለው ሁኔታ ጤፍን የመተካት አዝማሚያ እያሳየ በመሆኑን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በዚህ ወቅት አማራጭና ተኪ የሆኑ ምርቶችን በማምረት ገበያውን ማረጋጋት የሚቻል እንደሆነም ተናግረዋል። ሩዝ ገበያውም ጥሩ እንደሆነና ከማምረት አንጻርም እንዲሁ አርሶ አደሩ ከሌሎች ምርቶች በተሻለ ሁኔታ በሄክታር ማምረት እንደሚቻል ገልጸዋል።

የማዳበሪያና የቴክኖሎጂ አቅርቦት እጥረት ባለበት በዚህ ወቅት በክልሉ በሄክታር ከ40 እስከ 60 ኩንታል የሩዝ ምርት እየተመረተ መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አርሶ አደሩ ወደ ሩዝ ምርት በስፋት እየገባ መሆኑን አመላክተዋል።

# በክልሉ 19 ሚሊዮን ኩንታል የእንሰት ምርት ይጠበቃል

## - ከ100 ሚሊዮን በላይ የእንሰት ችግኞች ተሰራጭተዋል

አማን ረሺድ



አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በእንሰት ከተሸፈነው 203 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት 19 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ከ100 ሚሊዮን በላይ የእንሰት ችግኞች በክልሉ ለሚገኙ ለአርሶ አደሩ መሰራጨታቸውም ተገልጿል።

የክልሉ የግብርናና የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዑስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በእንሰት ከተሸፈነው 203 ሺህ 167 ሄክታር መሬት 19 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ በእንሰት ተክል ዙሪያ ከግብርና ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመቀናጀት በተሠራው ሥራ ተጨባጭ ውጤት ተገኝቷል።

እንሰት የምግብ ደህንነትና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ አይነተኛ ሚና አለው ያሉት አቶ ዑስማን፤ የእንሰት ተክል ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ጥሩ ውጤት እያስገኘ ነው ብለዋል።

የእንሰትን ምርታማነት ለማሳደግ ከአርሶ አደሮች ጋር በመቀናጀት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ክልሉ የሚታወቅበትን የእንሰት ተክል ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራዎች በቅንጅት በመሠራት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከድህረ ምርት ጋር በተገናኘ የሚያጋጥሙ ብክነቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን የገለጹት ኃላፊው የእንሰት ምርቶች በበሽታ እንዳይጠቁ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

በክልሉ በመማር ማስተማር ዘርፍ የተሠማሩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምርምሮችን በማድረግ የእንሰትን ጥቅም ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ እያስጨበጡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

እንሰት በየትኛውም የአየር ፀባይና መልከዓ ምድር የሚበቅል በመሆኑ ድርቅና የአየር ንብረት ለውጥ ችግር ለሚከሰትባቸው አካባቢዎች እፎይታ እንደሚሰጥ አቶ ዑስማን ጠቁመዋል።

የእንሰት ተክል ለተለያዩ ለምግብነት አገልግሎት እንደሚውል የገለጹት አቶ ዑስማን ለአጥሚት፣ ለገንፎ፣ ለዳቦ እና ለሌሎች አገልግሎቶች እንደሚውልም አስረድተዋል።


እንሰት የምግብና የሥነ-ምግብ ተስፋ ከማረጋገጥ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ-ምሕዳራዊ ጠቀሜታው ጉልህ መሆኑን ጠቅሰው በድርቅ ወቅት የዜጎችን ሕይወት በመታደግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

እንሰት የአረንጓዴ አሻራ ልማት አካል ተደርጎ እንደሚሠራ የጠቀሱት አቶ ዑስማን ለውጤታማነቱም በደቡብና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ከ100 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት መቻሉን አስረድተዋል።

የእንሰት ተክል ድህረ-ምርት ሂደትን ለማዘመን በቅርቡ ዓለም አቀፍ አውደ ጥናት መደረጉንም አቶ ዑስማን አስታውሰዋል።

# ዝምተኛው ተናጋሪ

ተስፋ ፈሩ



ድምፁ አይሰማም፤ መኖሩ ትዝ አይልም። በሁኔታዎች ግን ይናገራል። ከፍታ የለውም፤ መውረድ ብቻ ነው። ከሕይወት መሰላል ቁልቁል አምዘግዝጎ “የረገጡትን ያስጨብጣል”፤ ሳቅ አቅምሶ እምባ ያስውጣል።

አዋዝቶ ወዝ ያሳጣል፤ አስፈንጭቶ ያሳቅቃል፤ አሳስቆ ያስለቅሳል። “ውሃ የሚያደርግ ውሃ”፣ አጫሹን የሚያጨስ ጭስ፣ ቆማሪው ላይ የሚቆምር አታላይ፣ የማይደነዝዝ አደንዛዥ... የገዙትን የሚገዛ ጌታ ነው። አጅሬ ሱስ!

ሱስ እንደ ውሃ እያሳሳቀ ወስዶ፣ ውጥንቅጥ የግዞት ስብዕና ውስጥ ያሰጥማል። ዋኝቶ ወደ ነበሩበት ራስን የመግዛት ግዛት መጓዙ ብዙ ውጣ ውረድ አለው፤ የበረቱ ግን ያደርጉታል።

አቶ ባቱ የ53 አመት ጎልማሳ ነው። ከእድሜው እኩሌታ በላይ ለ 33 ዓመታት ሱስ ውስጥ ቆይቷል። የቀረው የሱስ አይነት እንዳልነበረ ሲገልጽ “ሳሙና መብላትና ሽቶ መጠጣት ነበር የቀረኝ” ሲል ይቀልዳል። ሱስ ብዙ ነገር አሳጥቶታል፤ የፊቱ ቆዳ ተበላሽቷል። የሚበላው ጫት ጊዜውን እንደበላበት፤ የሚጠጣው አልኮልም የሕይወትን ውሃ እንዳስጠማው የተረዳው ዘግይቶ ነው።

ያን ዕለት “በቃ” አለ። ቀሪ ዘመኑን ከሱስ የጸዳ ለማድረግ ወሰነ። ሱስ ለማቆም የተነሳሳው ትዳር መሥርቶ የአብራኩን ክፋይ ለማየት ባለው ጉጉት ነው። አዲስ ሕይወት የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ለሦስት ወራት ቆይቶ፣ ከብዙ ነገሮች ያዘገየውን ሱስ ተለይቶ ወጣ። ከማገገሚያ ማዕከሉ ከወጣ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ትዳር መሠረተ።

አሁን ከባለቤቴ ጋር ደስተኛ ሆኜ ሕይወትን እየመራሁ ነው የሚለው ባቱ፣ ሱስ ኑሮን የሚያምስ በሽታ ነው ይላል። ዛሬ በቤተሰቦቹ የሚሰጠውን ክብርና ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ሌላ መልክ ይዟል። ሱስ ውስጥ የነበረበት ዘመን ከዛሬው ጋር ሲያነጻጽር “ያኔ ማንም በሕይወት እንዳለ ሰው አይቆጥረኝም ነበር። ቤተሰቦቼም ተስፋ ቆርጠውብኛል። ሰው ፊት ለመቅረብ ስለምሸማቀቅ ሠርግ ቤት፣ ክርስትና እና ኃዘን ቤት አልገኝም ነበር።” ይላል።

ወጣቶችን “እንጠጣ እናጭስ ከሚል ጓደኛ ራቁ፤ የሱስ ጓደኛን ስልክ አሁኑኑ ‘ደልቱ’ “ ሲል ይመክራል። ሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ደግሞ “እኔን የገጠመኝ ዕድል እናንተንም ይግጠማችሁ” ብሎ ይመርቃቸዋል።

አቶ ነጋ (ስሙ የተቀየረ) ሱስ ውስጥ ለስምንት ዓመታት ቆይቷል። ደህና የኑሮ ደረጃ ካላቸው ቤተሰቦቹ ጋር ተጋጭቶ ጎዳና ላይ ለስምንት ወራት በኖረበት ወቅት ከሱስ ጋር እንደተዋወቀ ይናገራል። የጎዳና ልጆች የጎዳና ሕይወትን ለመርሳት የተለያዩ ሱሶች ውስጥ ይገባሉ የሚለው ነጋ፣ በብዛት ማስቲሽ ይስብ እንደነበርና አረቄ፣ ጫትና ሀሽሽም ሲጠቀም መቆየቱን ይገልጻል።

አሁን ከሱስ ለመላቀቅ ቆርጦ በአዲስ ሕይወት የሱስ ማገገሚያ ውስጥ ይገኛል። ወደ ማገገሚያው ከገባ ሦስተኛ ሳምንቱን ይዟል። ሰፈራቸው ውስጥ በሱስ በጣም የተጎዳ ልጅ ሆስፒታል ገብቶ ከሱስ መላቀቁን ሰምቶ ወደ ማገገሚያ ማዕከል ለመግባት መነሳሳቱን ይገልጻል።

ራሱን በስራ በመወጠር ለአራት ወራት ያህል ከሱስ ለመውጣት በግሉ ሙከራ አድርጎ አልተሳካለትም። አሁን ግን ከሱስ ለመውጣት ቆርጦ ወደ ማዕከሉ በመግባቱ በጣም ደስተኛ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቋቁሮ የነበረው ፊቱ ወደ ቀድሞ ይዞታው ተመልሶለታል።

“በሱስ ውስጥ መቆየት ራስን መጉዳት ነው። ጊዜህን ይገድልብሃል። በዕድሜህ መድረስ ያለብህ ቦታ ላይ እንዳትደርስ አድርጎ ከሰው በታች ያደርግሃል። እበልጣቸው የነበሩ እኩዮቼ እንኳን ጥለውኝ ሄደው ብዙ ነገር ይዘዋል። ብዙ ዋጋ ስላስከፈለኝ ሱስን ለጠላቴም አልመኘውም።” የሚለው ነጋ ከማገገሚያ ማዕከሉ ወጥቶ አዲስ ሕይወት ለመጀመር እንደሚጓጓ ይናገራል።

በአዲስ ሕይወት የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ያገኘነው ሌላ ጎልማሳ ደግሞ “ገንዘብ የሚገኘው በሃያ ልብ የሚገኘው በአርባ ዓመት” የተባለው ለእኔ ነው ባይ ነው። ሱስ ውስጥ የገባው የ22 ዓመት ወጣት ሳለ ነው። አሁን የ40 ዓመት ጎልማሳ ነው። ልብ ገዝቶ ለ18 ዓመታት ከከረመበት ሱስ ሊላቀቅ ጉዞ ጀምሯል። የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ከገባ 11ኛ ቀኑ ነው።

በአካባቢና በጓደኞች ተጽዕኖ ሱስ ውስጥ እንደገባ ይናገራል። የጫት፣ የሲጋራ፣ የማሪዋና እና የአልኮል ሱስ እንደነበረበት ይገልጻል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ነበር። በኋላ የሥራ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ እየሆነ በመምጣቱና ከአለቆቹ ጋር በመጣላቱ ሥራውን ለቋል። ለሱስ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የንግድ ማዕከል ከሆነው መኖሪያ አካባቢው ለማግኘት እየሞከረ ለሰባት ዓመታት ሰፈር ውስጥ ውሏል።

“ሱስ ራሱ ትዳር ነው” የሚለው ጎልማሳው በትዳር ላይ ትዳር መመሥረት ስለማይቻል እስካሁን እንዳላገባ ይናገራል። ከማዕከሉ ሲወጣ የተገኘውን ማንኛውንም ሥራ ሠርቶ ለመለወጥ ተስፋ የሰነቀው የቀድሞ መምህር፣ ሱስ በቁም በልቶ የሚጨርስ፤ ዝምተኛ ገዳይ መሆኑን በተለይ ወጣቶች ሊገነዘቡ እንደሚገባ ያሳስባል።

ዶ/ር አስካለማሪያም ቢክስ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የሕክምና ኮሌጅ የሥነ-አእምሮ ሐኪም ናቸው። እንደሚፈጥረው ጫና እና ሁኔታ የሱስ ሕመም ቀላል፣ መካከለኛና ከባድ ተብሎ እንደሚከፈል ይናገራሉ። ሱስ ከባድ ደረጃ ላይ ሲደርስ ተጠቃሚውን ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠር የገለጹት ዶክተር አስካለማርያም፣ “ሰውነት የለመደውን ነገር ካላገኘ ድብርት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ መነጫነጭና ጭንቀት እንዲሁም እንደ ሆድ ሕመምና መንቀጥቀጥ ያሉ አካላዊ ችግሮች ሊታዩ ይችላሉ” ብለዋል።

የሥነ-አእምሮ ሐኪሟ እንደሚናገሩት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተለመዱት ጫት፣ ሲጋራና አልኮል በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሕክምና ታዘው የሚወሰዱ እንደ ትራማዶልና ሞርፊን ያሉ መድኃኒቶችን የሚወስዱ ወጣቶችና ታዳጊዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። የተለያዩ የካናቢስ (ሀሽሽ) አይነቶች ተጠቃሚዎች ቁጥርም እያሻቀበ መጥቷል።

ሱስን “ሕይወትን ጠላፊ” ብለው የጠሩት ዶክተሯ፣ “ማኅበራዊ ግንኙነትን አውኮ፤ ተዓማኒነትንና ተቀባይነትን በማሳጣት ትልቅ ስነልቦናዊ ቀውስ ይፈጥራል። በመጨረሻ ለከባድ አእምሯዊና አካላዊ የጤና ችግሮች ያጋልጣል” በማለት ጓዙ ብዙ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሱስ ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ የጠቆሙት ዶ/ር አስካለማሪያም፣ “ሱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሱስ ሊታከም የሚችል ሕመም መሆኑን መረዳት አለባቸው። ሱስ ሕመም ነው ካልን ደግሞ እንደማንኛውም ሕመም ሊያገረሽ የሚችል ነው። እኛ ሁሌም ለታካሚዎቻችን የምንነግረው ማገርሸትን እንደ አንድ የመዳን ሂደት ተረድተው ትምህርት ወስደውበት እንደገና ወደ ለውጥ እንዲገቡ ነው። የሱስ ሕክምና በአብዛኛው የግለሰቡን ጥረት የሚጠይቅ ነው።” ይላሉ።

የአዲስ ሕይወት የሱስ ማገገሚያ ማዕከል መሥራች ሳይካትሪ ነርስ ይርገዱ ሀብቴ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሱስ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ እጥረት መኖሩን ያነሳሉ። ሱስ በገዛ እጅ የሚመጣ ነገር ነው ብሎ በማሰብ ግለሰቡ እንዲወጣው መተው ትክክል ስላልሆነ እንዲታረም ያሳስባሉ።

ሱስ በሽታ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል የሚሉት ሳይካትሪ ነርሷ፣ “ሱስ ውስጥ በገዛ እጅ ሊገባ ይችላል፤ ከሱስ መውጣት ግን የሌሎችን ድጋፍም ይጠይቃል።” በማለት እያንዳንዱ ሰው ከሱስ ውስጥ ለመውጣት ለሚታገሉ ሰዎች እገዛ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትንበያ በምሑራን ዕይታ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በቅርቡ ይፋ ባደረገው ትንበያ መሠረት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2024 የስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ እድገት እንደምታስመዘግብ ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ አሁናዊ ሁኔታዎች ማለትም የዋጋ ግሽበት፣ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል በሚወሰዱ ርምጃዎች፣ ዓለም አቀፍ ርዳታዎች መቀነስ፣ የብድር ጫና መጨመሩ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ግጭቶች እና የበጀት ፖሊሲ እንደፍላጎት አለመሆን በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት እያሳደሩ እንደሆነም ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ለዕድገቱ እንቅፋት ይሆናሉ ያላቸውን ሳይጠቅስ አላለፈም።

ለመሆኑ በነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ ስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ እድገት ማስመዝገብ እንዴት ይቻላል?

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዳዊት ሀየሱ (ዶ/ር) እንደሚሉት እ.ኤ.አ በ2024 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ ያድጋል ሲል ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ይግለፅ እንጂ ኢትዮጵያ ከስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ በላይ እድገት ማስመዝገብ ትችላለች። ይህንንም ለማድረግ በርካታ ምቹ ሁኔታዎች አሏት።

በተለይ ባለፉት ዓመታት የተሠሩ ሥራዎች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ በርካታ ለውጦችን አምጥተዋል ያሉት ዶክተር ዳዊት፤ አሁን ባለው ሁኔታ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በሦስት መዋቅር ከፍሎ መመልከት ይቻላል ብለዋል። እነዚህም በግብርናው ዘርፍ ያለው ምቹ ሁኔታ፣ በአገልግሎት ዘርፉ ያሉ ለውጦች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ያለው እምቅ አቅምንም ይጠቅሳሉ።

በግብርናው ዘርፍ በርካታ ምርት መስጠት የሚችሉ፤ ነገር ግን ያልታረሱ ሰፊ መሬቶች በኢትዮጵያ እንደሚገኙ በማንሳትም፤ መሬቶቹን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ማረስ ቢቻል የግብርናው ዘርፍ ከራስ አልፎ ለሌሎች ሀገራትም ጭምር መትረፍ የሚችል መሆኑን ያስረዳሉ፤ ይህም ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው መሆኑን ያነሳሉ።

የኢንዱስትሪ ዘርፉንም ብንመለከት እንደሀገር ለኢንዱስትሪ ግብዓት መሆን የሚችሉ በርካታ ምርቶች አሉ። ከዚህም ውስጥ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ከዓባይ ግድብ ጋር ተያይዞ ሰፊ እድል እየተፈጠረ ነው። ይህም የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛና ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል ባይ ናቸው።

የአገልግሎቱም ዘርፍ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገበ ነው። አየር መንገድ፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የመንግሥት ሥራዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉ መሆናቸው እና በሆቴሎች ሰፊ እድገት እየተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አንድ ኢንቨስተር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ማልማት እንዲችል ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ መሆናቸውን በማንሳት በኢኮኖሚው ዘርፍ ቀላል የማይባል አወንታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ናቸው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አሥር ዓመታት በየዓመቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስመዝግባለች። ይህ እንቅስቃሴ በአንድ ወቅት ተግዳሮት ቢያጋጥመው ኢኮኖሚያዊ እድገቱን ሊያዳክም አይችልም። አሁን ደግሞ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም እድገቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል። እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ኢትዮጵያ ከ6 ነጥብ ሁለት በመቶ በላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንድታስመዘግብ ያደርጋታል ሲሉ ይደመድማሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የዋጋ ግሽበት፣ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የሚወሰዱ ርምጃዎች፣ ዓለም አቀፍ ርዳታዎች መቀነስ፣ የብድር ጫና መጨመሩ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ግጭቶች እና የበጀት ፖሊሲ እንደፍላጎት አለመሆን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ነው የሚገልፁት። ሆኖም የሀገሪቱን እድገት ሙሉ ለሙሉ መግታት የሚችሉ አይደሉም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት በግጭት፣ በዋጋ ግሽበት እና በመሳሰሉት ጉዳዮች እንቅፋት ሊገጥመው እንደሚችል ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ያስቀመጣቸው ተግዳሮቶች የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት ሙሉ ለሙሉ ለመግታት ብቁ አይደሉም ያሉት ዶክተር ሞላ ሩሲያ ከዩክሬን ጋር በጦርነት ውስጥ ብትሆንም ኢኮኖሚዊ እድገት እያስመዘገበች መሆኑን እንደ አብነት አንስተዋል።

እንዲያውም የኢትዮጵያ አሁናዊ ሁኔታዎች ዘላቂ መፍትሔ ቢያገኙ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ከ10 እስከ 12 በመቶ እድገት ማስመዝገብ የሚችል መሆኑን ተናግረዋል።

ለዕድገቱ እንቅፋት ይፈጥራሉ ከሚባሉት አንዱ የዋጋ ግሽበት መኖሩ መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገራት የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የገንዘብ ፖሊሲ ይጠቀማሉ። ይህ ኢንቨስትመንትን የሚጎዳ በመሆኑ በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ነገር ግን በትብብር መሥራት ቢቻል በሁሉም ዘርፎች ውጤታማ ሥራዎችን መሥራት ይቻላል ብለዋል።

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ የሚያሳድገው በትብብር መሥራት ሲቻል ነው የሚሉት ምሑሩ፤ በትብብር ለመሥራት ደግሞ የባለሀብቱ፣ የሕዝብና የመንግስት ሚና ወሳኝ ነው። ከባለሀብቱ ገንዘብ፣ ከሕዝብ ግብዓት፣ ከመንግሥት ደግሞ የመሪነት ሚና ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት አስፈላጊ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ ዘንድሮ በኢኮኖሚ የታቀደውን ለማሳካት ትልቁ ዕድል የሰው ሃብት፣ የአየር ሁኔታ ምቹነት፣ በመስኖ የማልማት ሥራ መጀመሩ እንደእድል ይነሳሉ ያሉት ደግሞ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህርና ተመራማሪ ዱጋሳ ሙሉጌታ (ዶ/ር) ናቸው።

በዲፕሎማሲው መስክም በዓለም አቀፍ እና በቀጣናው በዲፕሎማሲው መስክ የተገኘው ቅቡልነትም ለገጽታ ግንባታ ይጠቅማል ብለው፤ ከዓባይ ግድብ ጀምሮ እየተጠናቀቁ ያሉ ፕሮጀክቶች እንደእድል ሊጠቀሱ ይችላሉ። የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶችም ለቱሪስት መስሕብ ትልቅ ዕድል እንደመሆናቸው ሌሎችን የቱሪዝም ዘርፉን ተመሳሳይ ዕድሎች አሚጥጦ መጠቀም ከተቻለ ትንበያው ስኬታማ መሆን ይችላል ባይ ናቸው።

በግብርናው መስክ የበጋ መስኖ ስንዴ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ የታየውን ማስቀጠል ከተቻለ ሌላው ተስፋ ሰጪ ሁኔታ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዶሮ፣ በከብት ርባታ የተጀመረውና የጓሮ አትክልት ከጤፍ፣ ገብስ፣ ከሩዝ፣ አጃና የበቆሎ ምርትን በማቀናጀት ከተሠራ በርግጥም ማሳካት ይቻላል ብለዋል።

ወደመካከለኛ ገቢ ለመሻገር የሚደረገውን ሂደት ለማሳካት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ይገባል። ለስኬቱ ቅድመ ሁኔታው ሰላም ማስፈን ተገቢ ነው። የሥራ ባሕል ካደገና ሰላም ከሰፈነ ደግሞ ከስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ በላይ ማስመዝገብ ይቻላል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የቱሪስት መስሕብ አላት፣ ሥራ ፈጣሪ ባለሙያዎች፣ የተፈጥሮ ሃብት፣ እውቀት፣ የባሕል ሃብት፣ ቋሚ ካፒታል ባለቤት እንደመሆኗ አቀናጅቶ መሥራት ለስኬቱ ቁልፍ ሥራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በተያዘው ዓመት ታስመዘግበዋለች ተብሎ በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት የተተነበየው የስድስት ነጥብ ሁለት በመቶ እድገትም ሆነ በመንግሥት የተቀመጠው የሰባት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ዕድገት በምሑራኑ ከተነሱ ሊፈቱ የሚችሉ ትናንሽ ችግሮች በስተቀር የጎሉ ችግሮች አልተነሱበትም። መንግሥት በዓመቱ መባቻ ላይ ቃል በገባው መሠረት በዚህ ዓመትም በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች በልዩ ትኩረት ከሠራ ዕቅዱን ማሳካት እንደሚችል ምሑራኑ ይስማሙበታል።

# በአማራ ክልል ተጥሎ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አሁን ላይ በክልሉ በተደረገ የሰላም ማስከበር ሥራ አንጻራዊ ሰላም መገኘቱን ተከትሎም ተጥሎ የነበረው የሰዓት እላፊ ላይ ማሻሻያ መደረጉን ተናግረዋል።

በዚህ መሠረትም በባሕር ዳር፣ ጎንደር እና ደብረ ብርሃን ከተሞች ሰዓት እላፊው ከነበረበት 2 ሰዓት ወደ 3 ሰዓት ከፍ መደረጉን ጠቅሰዋል። የሌሎቹ አካባቢዎችም በኮማንድ ፖስቱ እየተገመገመ የሚታይ መሆኑን ነው የገለጹት።

በባጃጆች ላይ የተጣለው ሰዓት እላፊ በጎንደር ከተማ እስከ 2 ሰዓት ከፍ ሲደረግ በሌሎቹ አካባቢዎች ግን እስከ 1 ሰዓት ሆኖ ይቀጥላል ብለዋል።

ኮማንድ ፖስቱ በክልሉ የፀጥታ ሁኔታ ላይ ግምገማ ያደረገ ሲሆን፣ በዚህም ኅብረተሰቡ ሰላም ወዳድ በመሆኑ ከፀጥታ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት አንፃራዊ ሰላም እንዲመጣ ሆኗል ብለዋል።



መንገሻ ፈንታው( ዶ/ር)

አሁን ላይ ከአንድ አንድ ራቅ ካሉ ወረዳዎች ውጪ ኅብረተሰቡ መደበኛ እንቅስቃሴውን ማድረግ መጀመሩም ተጠቅሷል ሲል ኤፍቢሲ ዘግቧል።

# አደጋ የደቀነው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ይናገራሉ። ከተካሄደው የፖለቲካ ሪፎርም በኋላ ዋናዎቹ የብዙኃን መገናኛዎች እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች በአንድ ጊዜ በጣም በተለጠጠ መልኩ ማንኛውም ሰው ሀሳቡን እንዲገልጽባቸው ሆነው ክፍት መደረጋቸው የፈጠረው ዕድል እንዳለ ሆኖ፤ ሀገር ላይ ብዙ አደጋዎችን መደቀኑን ይገልጻሉ።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አብዛኞቹ ሐሰተኛ መረጃዎች ሥራዬ ተብለው የሚሠሩ በመሆናቸው አቅጣጫ በማሳትና መረጃን በማዛባት ኅብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላሉ። ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲወዳደር ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት ተደራሽነት ውስን ቢሆንም ሐሰተኛ መረጃ በሚገርም መጠንና ፍጥነት እየተሰራጨ ነው። ማኅበራዊ ሚዲያው በባሕሪው ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸውን ሰዎች የሚሰበስብ በመሆኑ አንድ ሐሰተኛ መረጃ በብዙ ሰዎች ከተወደደና ከተጋራ ከእውነተኛው መረጃ ይልቅ ብዙዎች ጋር ይደርሳል።

ማኅበራዊ ሚዲያ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ዓላማው የማኅበረሰብን ትስስር ማጎልበት መሆኑን የሚያወሱት መምህሩ፤ አሁንም ድረስ በአውሮፓና አሜሪካ ያለው ሚና ይህ ነው። ከዓረብ የፀደይ አመጽ ወዲህ ግን በተለይ በአፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ ለተለየ ዓላማ እየዋለ ነው። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እያደረገ ባለው ጥናት የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ሚዲያ ይዘት ከ85 በመቶ በላይ ፖለቲካዊ ሆኖ ተገኝቷል ይላሉ።

አያይዘውም፤ "እንደ ዩቱዩብ ያሉ መተግበሪያዎች ክፍያ ስለሚፈጽሙ ሰዎች ለገንዘብ ሲሉ ሀገራቸውን የሚሸጡበት ሁኔታ መፈጠሩ የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት እንዲጨምር አድርጓል። ይህ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት በስፋት ታይቷል። የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ሚዲያ ለጦርነቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። ለጦርነቱ ሂደትና ውጤት ትክክለኛ ያልሆነ መልክ ሰጥቷል። አሁን ያለንበት ጦርነትም ከዚያ ጋር የተያያዘ ነው።" በማለት ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ትልቅ ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሐሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ አካላትን ተጠያቂ በማድረግ ረገድ የሕግ ክፍተት መኖሩንም ያነሳሉ። የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ታዋቂ ለሆኑ ሰዎች፣ ለፖለቲከኞችና ሃይማኖት መሪዎች ከለላ እንደሚሰጥ የሚጠቅሱት ዶክተሩ፤ "በተጨባጭ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች ስርጭት እንዲስፋፋ እያደረጉ ያሉት እነዚህ ሰዎች ናቸው። ግለሰቦችን የሚያነሳሱት የዝና፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ካባ የለበሱ ሰዎች ናቸው" ሲሉ ይተቻሉ።

አንተነህ (ዶ/ር) ትችት ያቀረቡበት የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ላይ "ልዩ ሁኔታ" በሚል የሰፈረው የአዋጁ ክፍል "አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር ወይም እንደ ሐሰት መረጃ ተወስዶ ማሰራጨት የማይከለከለው የትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር አካል እንደሆነ፤ የዜና ዘገባ፤ ትንታኔ ወይም የፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ፤ አልያም የኪነጥበብ፣ ትወና ወይም መሰል የሥነጥበብ ውጤት ከሆነ እንዲሁም የሃይማኖታዊ አስተምህሮት አካል እንደሆነ ነው።" ይላል።

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት የምርምርና ቴክኖሎጂ ዳይሬክተሩ ገብረክርስቶስ ኑርዬ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ሰዎች መረጃዎችን መረዳት ከሚገባቸው በታች አድርጎ ማሳነስ ወይም አግዝፎ ማጋነን እንዲሁም ሐሰተኛ የሆነውን እውነት፣ እውነት የሆነውን ደግሞ ሐሰት አድርጎ ማቅረብ ሐሰተኛ መረጃ ማሰራጨት ነው። ውጤቱም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል። ሥራዎችን ባወቅነው ልክ ስለሆነ የምንሠራው፣ የተሳሳተ ነገር ካወቅን የምንፈጽማቸው ተግባሮች በሙሉ የተሳሳቱ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ በሀገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል ይላሉ።

የምርምርና ቴክኖሎጂ ዳይሬክተሩ፤ ሐሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ አካላትን አሳካዋለሁ የሚሉት ዓላማ ኖሯቸው አቅደው የተሳሳተ መረጃ የሚያሰራጩ እና መረጃዎችን ሳያጣሩ ስህተት የሆነን ነገር ትክክል አድርገው የሚከተሉ በማለት ይከፍሏቸዋል።

ግብ ያላቸውን ሐሰተኛ መረጃ የሚያሰራጩ አካላት በሕግ ተጠያቂ ማድረግ እንደሚገባ የሚያሳስቡት ገብረክርቶስ (ዶ/ር)፤ ሳያውቁ የሚከተሉትን ወገኖች ግን እውነቱን ደጋግሞ በማሳየት እንዲታረሙ ማድረግ ይቻላል ሲሉ ይገልፃሉ።

መረጃ እንደ ምግብ አስፈላጊ የሆነበት ዘመን በመሆኑ መንግሥት በየጊዜው ትክክለኛ መረጃዎችን መደበኛ በሚባሉት የብዙኃን መገናኛዎች መስጠት መቻል እንዳለበት አስረድተው፤ ለጊዜው በሚስጥር መያዝ ያለባቸው ጥብቅ ሀገራዊ ጉዳዮች ከሆኑም ፍንጭ በመስጠት ወደፊት ጊዜው ሲደርስ በዘርዝር እንደሚገለጹ ማሳወቅ ይገባዋል ይላሉ።

የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ሥራ ላይ ካልዋለ መደንገጉ ብቻ ውጤት እንደማያመጣ ጠቅሰውም፤ ኅብረተሰቡ ያገኘው መረጃ ትክክል መሆንና አለመሆኑን ከተለያዩ ምንጮች ማረጋገጥ ይኖርበታል ሲሉ ይመክራሉ።

አንተነህ (ዶ/ር) በበኩላቸው በሚያቀርቡት የመፍትሔ ሃሳብ፤ "ሊንጉስቲክ" የሚባል በማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩ መልዕክቶችን መቆጣጠሪያ ዘዴ አለ። የማኅበራዊ ሚዲያ ልጥፎችን ከምስሎች ጀምሮ ቃል በቃል እያጣራ ተደጋጋሚ የሐሰት መረጃዎችን እና የጥላቻ ቃላትን በመቶኛ በማስቀመጥ የሚያሰራጯቸውን ግለሰቦች በመለየት ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል። መንግሥት በዚህ ላይ እየሠራ ነው። በአማርኛ ተሠርቶ አልቆ በኦሮምኛ፣ ትግሪኛ፣ ሶማሌኛ እና አፋርኛ ቋንቋዎች እየተዘጋጀ ይገኛል ይላሉ።

መወሰድ ያለባቸውን ተጨማሪ የመፍትሔ እርምጃዎች ሲጠቁሙም፤ መንግሥት ፌስቡክን እና ዩቱዩብን ከመሰሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያ አስተዳዳሪዎች ጋር በጋራ በመሥራት ኃላፊነት እንዲወስዱ ማድረግ መቻል አለበት። ተቋማትም ትክክለኛ መረጃ የሚሰጡበትን ይፋዊ ገጻቸውን በሚገባ በማስተዋወቅና ሐሰተኛ መረጃዎች ሲሰራጩ ፈጥነው እውነተኛውን መረጃ ለሕዝብ በማድረስ መታገል አለባቸው ይላሉ።

የሐሰተኛ መረጃዎች ሰለባ የሚሆነው ኅብረተሰብ መረጃዎችን ማጣራት እንዲችል ተደማጭ የሆኑ ሰዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች እና የትምህርት ተቋማት የኅብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና የሚጨምር ሥራ መሥራት ይኖርባቸዋልም ብለዋል።

ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚታየው ቀደም ሲል የነበሩን ኢትዮጵያዊ ባሕላዊ እሴቶች ወደ ኋላ የመቅረት ነጸብራቅ መሆኑን የገለጹት መምህሩ፤ በዋናነት እንደ መከባበር፣ መቻቻል እና አብሮነት ያሉ ኢትዮጵያዊ እሴቶች በብዙኃን መገናኛዎችና በትምህርት ሥርዓት ጎልብተው አንድነት ያለው ኅብረተሰብ እስካልተፈጠረ ድረስ የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት መቀጠሉ አይቀርም ሲሉ አሳስበዋል።

መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም. የጸደቀው የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ፣ ማንኛውም ሰው የሐሰት መረጃን በአደባባይ ስብሰባዎች፣ በብሮድካስት፣ በሕትመት ወይም በማኅበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሑፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ ተግባር መሆኑ ይደነግጋል።

# የቴክኒክና ሙያ ዘርፉን ለማሳደግ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ዶክተር ተሻለ አክለውም፤ በዚህ ዓመት ከ600 ሺህ በላይ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች ወደ ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ እንዲገቡ ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት በርካታ ቴክኖሎጂ የሚፈልጉ ናቸው ያሉት ዶክተር ተሻለ፤ በቴክኖሎጂው አቅም ያላቸው ሀገራትን በዘርፉ በማሳተፍ አቅርቦቱን በቀላል መንገድ ማሳለጥ ያስፈልጋል።

ዶክተር ተሻለ አክለውም፤ የልምድ ልውውጡ የቻይና የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ያላቸውን የካበተ ልምድ በመውሰድ ዘርፉን ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑን አስታውሰዋል።

የቻይና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ምክትል ሊቀመንበር ፕሮፌሰር ሰን ሻንገፑ በበኩላቸው የልምድ ልውውጡ ሰፊ ተሞክሮዎች መውሰድ የሚቻልበት በመሆኑ ለዘርፉ ማደግ ወሳኝ እንደሆነ ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር ሰን አክለውም፤ በመማር ማስተማር፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በመምህራንና በአመራር ሥልጠና ላይ የልምድ ልውውጦች ይደረጋሉ ብለዋል።

በሁለቱ ሀገራት የትምህርት ዘርፍ ለማሳደግ የቴክኒክ ሙያ ዘርፍ አንዱ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ሰን፤ የሁለትዮሽ ግንኙነቱ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማኅበራዊ ግንኙት ለማጠናከር እንደሚረዳ ጠቁመዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ሰን ገለጻ፤ የተደረገው የልምድ ልውውጥ በሁለቱ ሀገራት መካከል በዘርፉ የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ያግዛል።

ብሔራዊ የሥልጠና ግብዓት የመረጃ ቋት ማዘጋጀት፣ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ማመቻቸት፣ በጋራ ሥልጠናዎች የሚሰጡበት ሥርዓት መዘርጋት በትብብር ከሚሠሩ ጉዳዮች መካከል ናቸው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስአዝመራ መሰብሰቡ ሥራ ተገቢው ትኩረት ይሰጥ!

በአሁኑ ወቅት እንደ አግሮ ኢኮኖሎጂው ሁኔታ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የመኸር ወቅት አዝመራ መድረስ ጀምሯል። ይህንን የደረሰ የሰብል አዝመራ እንዲሁም በቀጣይ የሚደርሰውንም አዝመራ መሰብሰብ ደግሞ ወቅቱ የሚጠይቀው ትልቁ የግብርና ሥራ ነው።

ለዚህም እንደተለመደው አርሶ አደሩ፣ የግብርና ባለሙያው፣ ሌሎች ከግብርና ጋር ግንኙነት ያላቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የግሉ ዘርፍ ተቀናጅተው በትኩረት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም በሚደርሳቸው ጥሪ መሠረት በአዝመራ ስብሰባው እንደሚሳተፉ ተሞክሮዎች ያመለክታሉ።

እንደሚታወቀው የግብርናው ዘርፍ ለሀገራችን የምጣኔ ሀብት ዋና መሠረት ሆኖ ዘመናት አስቆጥሯል። ከዚህም የተነሳ ይህ ወቅት በተለይ ለአርሶ አደሩ ለዘመናት የትኩረት ስበት ማዕከል ሆኖ ቆይቷል።

አሁንም ቢሆን እንደ ሀገር በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል ከጀመርነው ሀገራዊ ጥረት አንጻር ወቅቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍ ያለ ትኩረት ተሰጥቶት፤ በኃላፊነት መንፈስ መሥራትን የሚጠይቅ እንደሆነ ይታመናል።

እንደሚታወቀው፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሀገሪቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት ተስፋ ሰጭ ስለመሆኑ በተጨባጭ እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶች ማሳያ ናቸው።

በተለያዩ አማራጭ የአስተራረስ ዘዴዎች እና ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ በጤፍ ምርት ላይ የታየው ምርታማነት፤ በበጋ ስንዴ እርሻ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያተረፈው ስኬት፤ የሩዝ እርሻን ለማስፋፋት እየተደረገ ባለው ጥረት የታየው መነቃቃት ...ወዘተ ለእነዚህ ሁነኛ አብነቶች ሆነው ይቀርባሉ።

ከዚህም ባለፈ በዘርፉ ያለውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በዘር የሚሸፈነውን ማሳ በየዓመቱ ለመጨመር እየተደረገ ያለው ጥረትና ይህን ተከትሎ እየተመዘገበ ያለው ውጤት አበረታች ሆኗል። በተያዘው የምርት ዘመንም 573 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ ነው። 17ነጥብ 3 ሚሊየን ሄክታር መሬት ለማረስ ታቅዶ 18 ነጥብ 8 ሚሊየን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን መቻሉን በቅርቡ የወጣ መረጃ ያመላክታል። ይህም ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት በዘር መሸፈኑን ያመለክታል።

ቴክኖሎጂንና ባለሙያን አቀናጅቶ በጋራ ለመጠቀምና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም ግብርናውን ትራንስፎርም ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ታምኖበት እየተሰራበት ያለው የኩታ ገጠም እርሻ እየተስፋፋ ይገኛል። በዚህ የመኸር ወቅት ስድስት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ያስተራረስ ዘዴ ለማልማት ታቅዶ፣ ስድስት ነጥብ 35 ሚሊየን ኩንታል ማረስ መቻሉንም መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአሲዳማነት የተጠቃን መሬት በማከም፣ እንደ በቆሎ ያሉ ሰብሎችን በእሽትነታቸው ለገበያ እንዲውሉ በማድረግና ማሳውን በሌላ ሰብል በመሸፈን፣ ረግረጋማ ቦታዎችን በማረስ፣ ወዘተ.. ከፍተኛ መጠን ያለው ማሳ በዘር ተሸፍኗል። በሰሜኑ ኢትዮጵያ ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ጦሙን ያድር የነበረ መሬት በዘር የተሸፈነበት ሁኔታም ተፈጥሯል።

በዚህ ሁሉ ርብርብ በዘር የተሸፈነው ማሳ አዝመራ አሁን እየደረሰ ይገኛል። ይህን አዝመራ በተቀናጀ መልኩ በርብርብ መሰብሰብ ቀጣይ ሀገራዊ የቤት ሥራ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህ ደግሞ ሰፊ የሰው ኃይል አሰማርቶ አዝመራ ከመሰብሰብ ጎን ለጎን ቴክኖሎጂን በሚቻለው አቅም አቀናጅቶ መጠቀም ይገባል፤ ይህም አዝመራን ፈጥኖ ከመሰብሰብ ባለፈ በምርት መሰብሰብ ወቅት የሚፈጠር ብክነትን ለመቀነስ ወሳኝ ነው።

ከዚህም ባለፈ በቅርቡ የወጣ የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት መረጃ እንዳመለከተው፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ ሊጥል ይችላል። ይህ መረጃ በራሱ ለአዝመራ ስብሰባው ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ አመላካች ነው።

በተለያዩ ዓመታት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በአዝመራ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል የመከላከያ ሠራዊት አባላትን፣ ተማሪዎችን፣ መምህራን፣ የከተማ ነዋሪዎችን ወዘተ..፣ በአዝመራ ስብሰባ እንዲሰማሩ በማድረግ ሰብል እንዲሰበስቡ ሲደረግ ኖሯል። አሁንም ከአየር ንብረት መዛባት ጋር ሊያጋጥም የሚችለውን ስጋት በተመሳሳይ መልኩ ለመፍታት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ብረትን ማስተካከል እንደጋለ !

ስሜነህ ደስታ

መንግሥት ሰፊ መሠረት ያለው፣ ፈጣን፣ ቀጣይነትና ፍትሃዊነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ልማትን አፋጥኖ ድህነትን በማስወገድ ብልጽግናን የማረጋገጥ ዓላማ ይዞ እየሠራ ይገኛል። ይህን ለማስፈጸም ደግሞ ትምህርት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ለዚህም ትምህርትን በየደረጃው ማስፋፋትና ጥራቱን ማረጋገጥ ግድ ይላል።

የትምህርት ጥራቱን በተመለከተ በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ መመልከት ከሚያስፈልግበት ደረጃ መድረሱን ያመላከተው በ2014ዓ.ም የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና ከኩረጃ ነጻ ለማድረግ በዩኒቨርሲቲዎች በልዩ ሁኔታ መካሄድ ሲጀመር ነው።

እንደሚታወቀው የ12ተኛ ክፍል ፈተና ውጤት ተፈታኞች አጠቃላይ ትምህርትን የሚያጠናቅቁበት፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ የሚሆነውን ውጤት ለማግኘት ፈተና የሚቀመጡበት ነው።

ከዚህ የተነሳም ፈተናውን ባልተገባ መልኩ ለማለፍ የተለያዩ ጥረቶች ይደረጋሉ፣ ፈተናውን ከመስረቅ ጀምሮ በኩረጃ ውጤታማ ለመሆን ብዙ ያልተገቡ ሥራዎች ይሰራሉ። በዚህም በተለያዩ ወቅቶች ፈተናው በራሱ ብዙ ፈተናዎችን ለማለፍ የተገደደበት ሁኔታ የቅርብ ትዝታ ነው። ፈተናዎችን ከመሰረዝ ጀምሮ የፈተና ቀናትን እስከ መለወጥ የደረሱ ችግሮች ተፈጥረዋል።

ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ የአፈታተን ሁኔታው ለኩረጃ እንዳይመች በማድረግ እየተደረገ ያለው ተግባራዊ ሥራ ተፈታኞች የራሳቸውን ውጤት የሚያገኙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት የቱን ያህል የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት ውስጥ እንዳለ አመላካች ሆኗል።

ለምሳሌ ከ2014 ዓ.ም. ለፈተና ከተቀመጡ ተማሪዎች መካከል ሃምሳ በመቶ እና ከዚያ በላይ የሚያመጡት ተማሪዎች 3.3 በመቶ ብቻ ነበሩ። ይህ አሃዝ በ2015 ዓ.ም. 3.2 በመቶ ወርዷል። ይህን ውጤት በመመልከት የትምህርት ሥርዓቱ ስብራት ምን ያህል የከፋ ስለመሆኑ መገመት አይከብድም።

ከዚህ በላይ የሚያሳዝነው ጉዳይ፣ በኩረጃ ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ያላቸው ተፈታኞች ትምህርት ሚኒስቴር ምንም ያህል የጠበቀ የፈተና አሰጣጥ አሠራር ቢከተል፣ እነሱም የፈተና አስተዳደሩን በግልም ሆነ በቡድን ለመፈተን የማይቦዝኑ መሆናቸው ነው።

በ2014 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን 20,170 ተፈታኞች እንዲሁም በ2015 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን 859 ተፈታኞች የፈተና አስተዳደር መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሰት ፈጽመው መገኘታቸውን ትምህርት ሚኒስቴር መስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ም. ባዘጋጀው መግለጫ አመልክቷል።

በ2015 ዓ.ም. የመመሪያና ድንጋጌዎች ጥሰት ከፈጸሙት ተፈታኞች መካከል 376 ተፈታኞች በቡድን 483 ተፈታኞች በግል ጥፋት ፈጽመዋል። በሁሉም ጥፋተኞች ላይ እንደተመዘገበው የጥፋት አይነት ከአንድ የትምህርት አይነት እስከ ሙሉ በሙሉ መሰረዝ ድረስ የሚደርስ ቅጣት ተጥሎባቸዋል።

የ2014 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን ተፈታኞች የመመሪያና ድንጋጌዎች ጥሰት ከ2015 ተፈታኞች ጋር ሲነጻጸር የ2015ቱ በእጅጉ ዝቅ ያለ ነው። ይሁን እንጂ አሁንም በቀጣይ አመሉ ያለባቸው ተፈታኞች ስልታቸውን ቀይረው፣ በግልም ይሁን በቡድን ተዘጋጅተው ብዛታቸውን ጨምረው የፈተና አስተዳደሩን ለመፈተን ሊመጡ ይችላሉና በተገኘው መሻሻል መዘናጋት አይገባም፤ ይበልጥ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል።

በሁለቱ ዓመት የተገኘው የ12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤት የትምህርት ሥርዓቱን ስብራት ለሁሉም ህብረተሰብ ፍንትው አድርጎ አሳይቷል። በዚህ ልክ ስብራቱ ይከፋል ተብሎ ባይታሰብም የትምህርት ሥርዓቱ ሊፈተሽና ሊስተካከል እንደሚገባው የወተወቱ አካላትም ጥናቶችም ነበሩ።

ለአብነት ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር (2008-2012 ዓ.ም.) ሰነድ ላይ፣ "የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት የትምህርት ውጤቶች የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ (EGRA)" በሚል በቀረበው ገጽ 26 ላይ የሚከተለው ተካቷል።

«በ2002 ዓ.ም. በሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ ነበር። ጥናቱ በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በቀጣይ ክፍሎች በአግባቡ ለመማር የሚያስችሏቸውን መሠረታዊ ክህሎቶች ያላዳበሩ መሆናቸውን አሳይቷል።

ለምሣሌ፣ ሁለተኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች 34 በመቶ ለደረጃው ከተዘጋጀው ምንባብ ውስጥ አንድም ቃል ማንበብ ሳይችሉ ቀርተዋል፤ ከተማሪዎቹ 48 በመቶው ከተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ፈተና አንዱንም መመለስ አልቻሉም፣ በተጨማሪ ከተማሪዎቹ መካከል በደቂቃ 60 ቃላትን አቀላጥፈው ማንበብ (ተማሪዎች በደቂቃ 60 ቃላት እንዲያነቡ ይጠበቅ ነበር) የቻሉት 5 በመቶ ብቻ ናቸው። »

ይህ የሚያሳየው የትምህርት ስብራቱ በትምህርት ባለሙያዎቹ ቀደም ሲልም የሚታወቅ መሆኑን፣ በዚያው ልክ ግን በከፍተኛ ደረጃ ባሉ የትምህርት አመራሮቹ ተግባራዊ የመፍትሔ ርምጃ አለመወሰዱን ነው። አሁን በ12ተኛ ክፍል ተፈታኞች ላይ ትምህርት ሚኒስቴር ከበፊቱ የተለየ የፈተና አስተዳደር መመሪያ ድንጋጌዎች በማውጣት ወደ ተግባር ሲገባ ቀደም ሲል የነበሩ የትምህርት ጥራት ችግሮች በአስደንጋጭ ደረጃ ታይተዋል።

አሁንም ቢሆን የነበረው ችግር ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር የተማሪዎች በፈተና ዝቅተኛ ውጤት የማምጣት ሁኔታ በቀጣይ ዓመታትም ሊቀጥል አለመቻሉ ማስተማመኛ ነገር የለም፤ የሚሻለው ግን ተስፋ ባለመቁረጥ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የትምህርት ጥራትን የሚያስጠብቁ ተግባራትን ተግቶ መሥራት ነው።

በ2015 ዓ.ም. ተግባራዊ የሆነው በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ለመጀመሪያ ዲግሪ እጩ ተመራቂዎች የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና መሰጠቱ እንዲሁም በ2016 ዓ.ም. የተጀመረው ለሁሉም ሁለተኛ ዲግሪ አዲስ ተመዝጋቢዎች ትምህርት ሚኒስቴር በማዕከል በሚያወጣው የመግቢያ ፈተና ተመዝነው ሲያልፉ ብቻ ትምህርት የሚጀምሩ መሆኑን ስንመለከት ይበል የሚያስብል ተግባር መሆኑን እናስተውላለን።

በ12ተኛ ክፍል የተጀመረው የምዘና ሥርዓት ወደታች ስድስተኛ እና ስምንተኛ ክፍልም ችግሮችን ወረድ ብሎ በማየትና በማጥናት ጠበቅ ያለ የምዘና ሥርዓትን በመዘርጋት ችግሮቹን መፍታት ይገባል።

ብረትን መቀጥቀጥ(ማስተካከል) እንደጋለ ነውና በሁለተኛ ደረጃ እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተጀመረው የትምህርት ሥርዓት ማስተካከያ ወደ አንደኛ ደረጃም በተያዘው ግለት መዝለቅ አለበት። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለውን የትምህርት ሂደት ስንቃኝ ተማሪዎችን ወደ ቀጣዩ ክፍል ማሳለፍ እንጂ ብቁ የማድረጉ አሠራር ትኩረት ተነፍጎት ይስተዋላል።

የትምህርት አመራሮችና መምህራን «ከመንግሥት የተሰጠን መመሪያ ተማሪዎችን አብቅቶ ማሳለፍ እንጂ መጣል እንደማይቻል ነው» ይላሉ። ይህ አሠራር ዋነኛ ዓላማው በትምህርታቸው ደከም የሚሉ ተማሪዎችን ከመጣል ይልቅ የክለሳ ትምህርት በመስጠት ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ አድርጎ ወደ ቀጣዩ ክፍል ማሸጋገር ነው።

አሠራሩ ከቃል በዘለለ ተግባራዊ ቢደረግ ብቁና ተወዳዳሪ ተማሪዎችን ከለጋነት ዕድሜያቸው ጀምሮ ማፍራት የሚያስችል ቢሆንም አስተዳዳሪዎቹና መምህራኑ ግን ስንት ተማሪ አሳልፌ ከተጠያቂነት ዳንኩኝ እንጂ፣ ስንት ተማሪ አበቃሁ የሚል አሠራራቸው የደከመ መሆኑ ይነገራል። በመሆኑም የዚህን አሠራር አተገባበር በጥናት በመፈተሽ የመፍትሔ ሥርዓት ማበጀት ይገባል።

በ2015 ዓ.ም. መጨረሻ በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የትምህርት ንቅናቄ በማካሄድ በተለያዩ ድርጅቶችና በግለሰብ ባለሀብቶች በከፍተኛ ቁርጠኝነትና የእኔነት መንፈስ ብዛት ያላቸው ትምህርት ቤቶችን የማደስና የትምህርት ግብዓቶችን የማሟላት ተግባር ተከናውኗል። ይህ ሥራ በትምህርት ቤቶች ደረጃ ማሻሻል ሀገራዊ ንቅናቄ ተፈጥሮበት እየተሠራበትም ይገኛል።

ተግባሩ ቀጣይነት ቢኖረው፤ ትምህርት ሚኒስቴርም የትምህርት ሥርዓቱን ከትምህርት ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ጥናት በማድረግ ችግር ፈቺ በሆነ ሁኔታ ሥርዓት ቢያበጅለት፤ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና መምህራን ሙያቸውን በአግባቡ ከመወጣት በተጨማሪ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተሳለጠ ሁኔታ እንዲከናወን ከተማሪዎች፣ ከወላጆች እንዲሁም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል።

ወላጆችና አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ምክርና ቁጥጥር በማድረግ እገዛ ቢያደርጉላቸው፤ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመማር መምህራንና ወላጆች የሚሰጧቸውን ምክርና አስተያየት በአግባቡ በማዳመጥ ቢተገብሩ፤ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ለትምህርት ጥራት የበኩሉን አስተዋጽኦ ቢያደርግ፤ በየክፍል ደረጃው የትምህርት ጥራት እየተጠበቀ ይሄዳል።

ይህ ተግባር በተጠናከረ መልኩ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የሚተገበር ከሆነ አሁን የምናየው አስደንጋጭ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል የፈተና ውጤት በአጭር ጊዜ ውስጥ አስደንጋጭ ወደማይሆንበት ደረጃ ይቀየራል፤ ወደፊት የተሻለ ደረጃ ላይ ይደርሳል። የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሶ ለማየት ግን ብረትን መቀጥቀጥ(ማስተካከል) እንደጋለ ስለሆነ በተያዘው የተነሳሽነት ግለት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ትምህርት የሁሉ ነገር መክፈቻ ቁልፍ፣ የሀገር እድገት ወሳኝ መሳሪያ መሆኑን በመረዳት ለትምህርት ሥርዓቱ ጥራት መጠበቅ የሚጠበቅበትን ተግባር ለማከናወን ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል።

# ቀይ ባህር የአብሮ ማደግ ተስፋ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከሰሞኑ ሀገራዊ መነጋገሪያ አጀንዳ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የቀይ ባህር /የወደብ/ ጉዳይ ፊተኛ ነው። በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሕዝብ እንደራሴዎችን ሰብስበው ስለጉዳዩ አጽንኦት ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ሰፊ ሽፋን ያገኘ ሆኗል። ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት ፍላጎት በሕዝብ እንደራሴዎች ፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተነሱ እና ከተተነተኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ቀዳሚው ነው።

የቀይ ባህር ጉዳይ አጽንኦት ተሰጥቶት ርዕስ ከመሆን ባለፈ ወደተጨባጭ እውነታ እንዲመጣ ያደረገው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። የመጀመሪያው የሀገራችን የሕዝብ ቁጥር አሰፋፈርና በየዓመቱ እያደገ የመጣው የሕዝብ ቁጥር ምጣኔ ነው። ከቀይ ባህር እና ከህንድ ውቅያኖስ አቅራቢያ መገኘታችን የባህር በር ጥያቄያችንን ምክንያታዊ ከማድረጉ ጎን ለጎን ተዓማኒነት ያለው ያደርገዋል።

ይሄን በመሰለው ተፈጥሯዊ ሁኔታ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ላይ ያነሳችው ጥያቄ በበጎ ጎኑ ሊታይ የሚችል፤ አሁን ካለው የሕዝብ ቁጥርና የፍላጎት መናር አኳያ ደግሞ እንደህልውና ሊታይ የሚችልም ነው።

በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ታሪክ ውስጥ ቀይ ባህርን እና ዓባይን ለይቶ ማየት አይቻልም። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሕዝብ እንደራሴዎች ፊት የተሰማውን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ንግግር መጥቀስ ይቻላል። ‹ቀይ ባህርና ዓባይ ኢትዮጵያን የሚበይኑ፣ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የተቆራኙ፣ ለኢትዮጵያ እድገትና ጥፋት መሠረት የሚሆኑ ናቸው። ከዚህ የተነሳም ከርዕሱ መሸሽ አይቻልም።

እውነት ነው ታሪካችን ከተፈጥሮ ሀብት ጋር የተቆራኘ ነው። ይሄን የተፈጥሮ ሀብት በነጻነትም ሆነ በይገባኛል መንፈስ ስንጠቀመው አንታይም። የአፍሪካ የውሃ ገንቦ የሚል ቅጽል ስም የወጣላት ሀገራችን ተፈጥሮ ሀብቶቿን እንዳትጠቀም የነበረውን ጫናና ጣልቃ ገብነት ሁላችንም የምናውቀው ነው።

በርግጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለማመልከት እንደሞከሩት፤ በውሃ ተከቦ ውሃ መጠማት ዘመኑን የማይመጥን፣ ለትውልዱ ምክንያታዊ ሆኖ የሚቀርብ ምላሽ የማያስገኝ እሳቤ ነው። የትኛውም ሀገር ተፈጥሮ ሀብቱን ለፈለገው አላማ በኃላፊነት መንገድ የመጠቀም መብት አለው። ይሄን መብት ለማረጋገጥ አንቀጽ መጥቀስም ሆነ ስምምነት መፈራረም እምብዛም የሚያስፈልገው ሆኖ አይገኝም። አሁን ባለው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ወሳኙ ነገር ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደርግ ውይይት መግባባት ነው።

ከቀይ ባህር ጋር የተያያዘውም ሰሞነኛ አጀንዳ መነሻው ውይይት ነው፤ መድረሻው የጋራ ተጠቃሚነት ነው። በውይይትና ታሪክን መሠረት ባደረገ የተግባቦት መርህ ካልተኬደ የሚጠበቀውን የአብሮ ማደግ ምኞት ላይጸንስ ይችላል። ከፖለቲካና ከብቻ ተጠቃሚነት ወይም ደግሞ፤ ከአንዳንድ አሉባልታዎች ለማጽዳት መነሻና መድረሻውን አላማና ግቡን ብዙኃነት ማድረግ የተሻለ እምርታን ያመጣል።

የጋራ ተጠቃሚነት በአንድ ሀገር የበላይነት ወይም ደግሞ ተጽእኖ ፈጣሪነት ሳይሆን ሁሉንም ማዕከል ባደረገ የአብሮ መልማት መርህ የሚሆን ነው። በቀይ ባህር ላይ የተነሳው ወቅታዊ ጥያቄም ከዚህ አንጻር የሚቃኝ ነው። የህዳሴ ግድባችንን ስንጀምር የነበረው ንትርክና ሰጣ ገባ የሚታወስ ነው። የባህር በር የማግኘቱ ጥያቄም ከዚህ እውነታ ጋር ተቆራኝቶ የሚታይ ነው።

በቀይ ባህር ጉዳይ በጋራ ተጠቃሚነት መግባባት ላይ መድረስ ይቻላል። አሁን

**ከኢኮኖሚያዊ አመክንዮ አንጻር ሲታይ የሀገር ህልውና ጥያቄ መሆን የሚችል ነው። በአንድ ሀገር ላይ ለድህነት እንደ ምክንያት ከሚወሰዱ መነሻዎች ውስጥ የባህር በር ከ20 እስከ 30 ከመቶ የሚሆነውን የሚይዝ ነው። ከመጪው ዘመን ሁለንተናዊ ፍላጎት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ፣ ለድህነትም ሆነ ለእድገት እንደዋነኛ መነሻ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ከማደግና ከመልማት የብዙኃነት መሻት ጋር ትስስር ያለው የተስፋና የብሩህ ነገ መነሻ ነው**

የሚሰማው የባህር በር የማግኘት ጥያቄ ራስ ወዳድ ወይም ደግሞ ጊዜውን ያልጠበቀ ጥያቄ ሳይሆን በብዙኃነትና በፍላጎት በሕዝብ ቁጥሯም እያደገች ለመጣችው ሀገራችን እጅግ የዘገየ ጥያቄ ነው። አብሮ ከማደግ ጎን ለጎን ጉርብትናን የሚፈጥር፣ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በማህበራዊ ሕይወታችን እርስ በርስ የሚያስተሳስር ሌላው የአብሮነት ተምሳሌት ነው።

አንዳንዶች እንደሚሉት ትኩሳትን የሚፈጥር ሳይሆን የትውልዱን ጥያቄ፣ ፍላጎትና መሻት የሚመልስ፣ እኛ ያለንን ለሌሎች በመስጠት ሌሎች ያላቸውን ለእኛ በማካፈል የትብብር መንፈስን የምንፈጥርበት የትስስር በር ነው። ዛሬ ብቻ ሳይሆን ነገ ለሚመጣው ትውልድና ፍላጎት የመኖር ዋስትና ከመሆን አኳያ የላቀ ዋጋ ያለው ነው።

ዓለም ላይ የባህር በር የሌላቸው ወደ 44 የሚጠጉ ሀገራት አሉ። አስገራሚው ነገር ከነዚህ ሀገራት ውስጥ ብዙ የሕዝብ ቁጥር ይዛ የባህር በር የሌላት የእኛ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት። በአፍሪካም ስናየው ተመሳሳይ ነው። በአህጉሩ ካሉ 17 የሚሆኑ ወደብ አልባ ሀገራት የሕዝብ ቁጥራቸው ተደምሮ የእኛን የማያክልበት አስገራሚ ሁኔታ አለ። ፍትህና እውነት በነገሰበት ፖለቲካ ጥላ ስር ብንሆን ያነሳነው ጥያቄ ተገቢ ነው። የማንንም ለመውሰድ ጥያቄ አላነሳንም። ታሪክ የሚያውቀውን በጊዜ ሂደት የራቀንን እውነት ለመመለስና አብሮ ለመጠቀም ነው።

የባህር በር ጥያቄ አንድ ነጠላ ትርጉም ያለው ሳይሆን ሰፊና በብዙ አቅጣጫ ሊታይ የሚችል ጉዳይ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በማደግ ላይ ላሉና ብዙ ተስፋን ለሰነቁ ሀገራት ሚናው የት የሌለ ይሆናል። ከዘርፈ ብዙ ጠቃሚነቱ ጥቂቱን ብናይ፤ ‹ከጠብታ ውሃ እስከ ባህር ውሃ› በሚለው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ንግግር ላይ በስፋት ተነስቶ ለእንደራሴዎች የቀረበበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል።

ከኢኮኖሚያዊ አመክንዮ አንጻር ሲታይ የሀገር ህልውና ጥያቄ መሆን የሚችል ነው። በአንድ ሀገር ላይ ለድህነት እንደ ምክንያት ከሚወሰዱ መነሻዎች ውስጥ የባህር በር ከ20 እስከ 30 ከመቶ የሚሆነውን የሚይዝ ነው። ከመጪው ዘመን ሁለንተናዊ ፍላጎት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ፣ ለድህነትም ሆነ ለእድገት እንደዋነኛ መነሻ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ከማደግና ከመልማት የብዙኃነት መሻት ጋር ትስስር ያለው የተስፋና የብሩህ ነገ መነሻ ነው።

ከፖለቲካ እና ደህንነት አኳያ ሲተነተን ዘርፈ ብዙ አበርክቶ ያለው ነው። ከሉዓላዊነት አንጻር የሀገርን ሚስጢር ለመጠበቅ፣ ከተለያዩ የእቀባ ተጋላጭነት ለመዳን፣ ተፎካካሪ ኃይል ለመፍጠር እና በቀይ ባህር ፖለቲካ ላይ ወሳኝ ሚና ያለው ለመሆን የላቀ ሚና አለው። በታሪክ እና በትርክት መነጽር ስንቃኘው ደግሞ አሁናዊ ብዥታዎችን የሚያጠራ እውነትን እናገኛለን። ቅድመ ቅኝ አገዛዝ ኢትዮጵያ የባህር በር ነበራት። በአክሱም ዘመነ መንግሥት ሰፊ ግዛት ስለነበራት አዶሊስ የሚባል የባህር መተላለፊያ ነበራት። ይህን ወደብ በመጠቀም ከእስያ፣ ከሰሜን አፍሪካና ከጎልፍ ሀገርት ጭምር የንግድ እንቅስቃሴ ታደርግ ነበር።

በጊዜው በነበረው የባህር በር የአክሱም ስልጣኔ በዓለም ላይ ካሉ ፈር ቀዳጅ ስልጣኔዎች አንዱ ነበር። ለዚህ ስልጣኔ መነሻ ተደርገው የሚወሰዱት ደግሞ በባህር በር በኩል የተስተናገዱ የንግድ ልውውጦችና ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተደማጭነቶች ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የታሪክ ተመራማሪው አየለ በከሪ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ ላይ የባህር በርን በተመለከተ ‹የባህር በር ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት መረጋገጥ ወሳኝ ነው›።

የቀይ ባህር ጉዳይ ከኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህል፣ አኗኗር፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ጋር የነበረው ቁርኝት ጥብቅ እንደነበር ወደኋላ መለስ ብሎ ታሪክን ማስታወስ ያሻል። ጥንታዊ ስልጣኔዎቻችን ከዓለም ታላላቅ ሀገራትና ስልጡን ማህበረሰቦች ጋር በንግድና በሌሎች መስኮች መስተጋብር እንደሚያደርጉ ታሪክ አለን። እንደ ታሪክ አተያይ የትላንትዋ ባለ ወደብ ሀገር ዛሬ ላይ ለጎረቤት ሀገራት ብዙ ዶላር እየከፈለች እንድትገለገል ያደረጋት የራሱ የሆነ የተዛባ ትርክት ቢኖረውም እውነቱ ግን ቀይ ባህርና ኢትዮጵያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው የሚለው ነው።

ወደቀደመ ስማችን እንድንመለስ የራሱ የሆነ የተግባቦት አካሄድ ቢኖረውም ውይይትና መሰል የሰላም አማራጮች ግን ከየትኛውም በላይ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ከእርጋታና ስክነት በላይ አርቆ ማሰብን የሚጠይቁ ናቸው። በእርጋታና በስክነት አርቆ በማሰብም የጥያቄዎቻችንን ምላሽ መጠበቅ ከጋራ ተጠቃሚነት አንጻር የሚመከር ነው።

የባህር በር ባለቤትነትን ወይም ደግሞ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ርምጃ ውይይት ነው። ከውይይት ውጭ ለምንም ምቹ ባልሆነ ዘመን ላይ ነን። ለእንዲህ ዓይነቱ የጋራ ህልውና በጋራ ከመምከር ባለፈ ሌላ የተግባቦት አማራጭ የለም። የኃይል ርምጃ ትውልዱን ቁርሾ ውስጥ አሊያም ደግሞ በአብሮነት የዳበረውን ጉርብትና ከማጠልሸት ባለፈ ለማንም የሚበጅ አይሆንም።

ለዚህም የባህር በር ባለቤትነትን በተመለከተ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተነሱ አንዳንድ የአካሄድ መርሆችን ማንሳት ይቻላል። የመጀመሪያው የይገባኛል ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ማቅረብ ነው። ይሄ መርህ ከላይ ካወራነው የውይይት ጽንሰ ሃሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው። ሌላው የጋራ ተጠቃሚነትን ማዕከል ያደረጉ ሰላምና አንድነት ፈጣሪ ሃሳቦችን መለዋወጥ ነው።

ይሄም ከመነሻ ሃሳባችን ጋር የሚስማማ ሁሉን አቃፊ ምክር ነው። በመቀጠል ከቅደመ ቅኝ ግዛት ይልቅ አሁናዊ የአብሮ መሥራትን ተጠቃሚነት ማስቀደም ነው። እንዲሁም ደግሞ በፍትህና በርትዕ ላይ የተመሰረተ ግብን መጥቀስ ሌላኛው የአካሄድ መርህ ሲሆን በመጨረሻም በኢኮኖሚያዊና በሕዝብ አሰፋፈር የተደገፈ ፍላጎትን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳው ሌላው ነገር ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት ነው። የባህር በር ጥያቄ የአንድ ግለሰብ ወይም ደግሞ የአንድ ፓርቲ ጥያቄ ሳይሆን ሁለንተናዊ መልክ ያለው ነው። በዚህም ማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ንቃትና ዝግጁነትን በእጅጉ ይጠይቃል። ሌላው ከዚህ ጋር የተነሳው ዲፕሎማሲያዊ አካሄዶች ናቸው። ከጉዳዩ ጋር ልምድና ተሞክሮ ያላቸውን መልዕክተኞች መሰየም እንደዚሁ የተነሳ ሃሳብ ነው። አጀንዳውን አፍሪካዊ ማድረግና የሩቅ እና የቅርብ ወዳጅ ሀገራትን ይሁንታ ማግኘት በባህር በር ጉዳይ ላይ ልዩነት የምናመጣበት አካሄድ እንደሆነ ተጠቁሟል።

ይሄን በመሰለው አካሄድ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሀገራት ጋር ለውይይት መቀመጥ ተቀባይነት ለማግኘት የተሻለው መንገድ ነው። ቀጣይ በሚኖረው ሂደትም የወደፊቱን የተስፋ ብርሃን እንመለከታለን የሚል የጋራ ሃሳብ አለን። በውሃ ተከበን ውሃ መጠማታችን በህዳሴ ግድባችን ታሪክ እንደሆነ በወደብ ተከበን ወደብ ማጣታችንም የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ ውይይት ምላሽ እንደሚያገኝ ተስፋ እናደርጋለን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የመኸር ወቅት እርሻ ሥራው አበረታች ውጤት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ በዓለም በግብርና እና በምግብ መስክ ጥሩ የአየር ንብረት እና ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ፣ ሰፋፊ የእርሻ መሬት እና የተትረፈረፈ የውሃ ሀብቶች ካሉባቸው ጥቂት የዓለም ሀገራት አንዷ እንደሆነች ይገለጻል። ሀገሪቱም እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም በ2023 በግብርናው ዘርፍ በዓለም ላይ ካሉ አምስት ታላላቅ አምራች ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ማቀዷን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህን ዕቅድ ለማሳካትም የበጋ መስኖ ሥራን ጨምሮ በዘርፉ በርካታ ተግባሮች እየተከናወኑ መሆናቸውን የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እያከናወናቸው ባሉ ተግባራት አበረታች ውጤት እንደሚጠበቅ ጠቁሟል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሰሞኑ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መምጣቱን አስታውቋል። በቀጣይም የዘርፉን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከማዳበሪያ ዝግጅትና ከምርጥ ዘር አቅርቦት ጋር ተያይዞ እንዲሁም በሰብል እንክብካቤና በሌሎችም በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ገልጿል። በ2015/16 የምርት ዘመን የተሻለ ውጤት እንደሚመዘገብም ተመላክቷል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶክተር) የበልግ እርሻ ወቅት አፈፃፀምን አስመልክተው እንደተናገሩት፤ በ2015 ዓ.ም የበልግ እርሻ በነበረው የዝናብ ሥርጭት በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች (በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሲዳማ ደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልሎች) ጥሩ ጊዜ ነበር። በዚህም ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ በዋና ዋና ሰብሎች (በስንዴ፣ በበቆሎ፣ በገብስ፣ በማሽላ እና በሌሎች ሰብሎች) ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

እስካሁን ባለው ጊዜ በሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ያለ አዝመራ መሰብሰቡን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ ከዚህም ከ48 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል ብለዋል። አዝመራው በአሁኑ ወቅት ተሰብስቦ እንዳላለቀና ያልታወቀ ምርት እንዳለም ተናግረው፣ የምርት መጠኑ ሊሻሻልና ሊጨምር እንደሚችል ነው ያመላከቱት። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለው ግምገማ መሠረት ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በዘንድሮ በጀት ዓመት የበልግ ወቅት በመሬት ስፋትም ሆነ በምርት ይዘት ጥሩ ውጤት መመዝገቡን ተናግረዋል።

የ2015/16 የምርት ዘመን የመኸር ወቅት የግብርና ሥራ የተሻለ መሆኑንም ሚኒስትሩ አስታውቀዋል፤ በዚህ የምርት ዘመን የመኸር ወቅት 17 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አካባቢ ለማረስ ታቅዶ 18 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከዕቅድ በላይ ማረስ መቻሉን ተናግረዋል።

ይህ አሃዝ ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር ብልጫ እንዳለው አመልክተው፣ ለዚህም አንዱ ምክንያት ባለፉት ሁለት ዓመታት በትግራይ ክልል በመኸር ወቅት በዘር ያልተሸፈነው አንድ ሚሊዮን ሄክታር አካባቢ መሬት ዘንድሮ በዘር በመሸፈኑ መሆኑን ጠቅሰዋል። ሁለተኛው ምክንያት በተለያዩ አካባቢዎች ከዚህ ቀደም ከሚታረሰው መሬት ተጨማሪ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር የተሸፈነበት ዓመት በመሆኑ ነው ብለዋል።

በመኸር ወቅት 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን መቻሉን ጠቅሰው፣ በዚህም ዕቅዱን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት መቻሉን አስታውቀዋል። በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታሩ በክላስተር ወይም በኩታ ገጠም እርሻ መሸፈኑን አመላክተዋል። ኩታ ገጠም ወይም ክላስተር ባለፈው ዓመት ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ እንደነበረ አስታውሰው፤ በእዚህ ዓመት ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ጭማሪ ማስመዝገብ መቻሉን አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ ምርታማነትን ለማሳደግ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ባለፉት ዓመታት የተጠናከረ ሥራ ተሰርቷል። በተለይም የኩታ ገጠም ወይም የክላስተር እርሻ እየሰፋ መጥቷል። ይህም በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን፤ አርሶ አደሩ ለፍጆታ ከሚያመርተው ምርት ባለፈ ቴክኖሎጂንና የተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽኖችን በመጠቀም ተሰባስቦ ማምረቱ ለኢንዱስትሪና ለኤክስፖርት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ምርቶችን በጥራትና በብዛት ማምረት አስችሎታል። ይህም በኢትዮጵያ ግብርና አሰራር ሥርዓት ውስጥ ከተመዘገቡ ለውጦች መካከል አንዱና ወሳኝ ለውጥ ተብሎ ሊወሰዱ ይችላል፡፡

የኩታ ገጠም እርሻ ተጠናክሮ የቀጠለና ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር የደረሰ ቢሆንም ሜካናይዝድ ሆኖ በትራክተር የታረሰው መሬት አራት ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ሜካናይዜሽን ላይ ገፍቶ መሄድ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ ኩታ ገጠም እርሻ መሬትን ለሜካናይዜሽን የተመቻቸ ያደርጋል። ትራክተርና ኮምባይነር ያላቸው የተበጣጣሰና የተራራቀ ቦታ ላይ ከመሥራት ይልቅ አንድ ቦታ ላይ 100 እና 50 ሄክታር ቦታ ላይ ለመሥራት ያስችላቸዋል። ይህም የማሽነሪ ፍላጎት እንዲጨምር ያደርጋል። ሜካናይዜሽኑ አሁንም ግማሽ ላይ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ለዚህም ተጨማሪ የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን ማስገባትና ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራዎች በቀጣይነት መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡

ከሜካናይዜሽን አንጻር በየዓመቱ መሻሻል ስለመኖሩ ያነሱት ሚኒስትሩ፤ ባለፈው ዓመት ሁለት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት አካባቢ በሜካናይዜሽን መታረሱን አስታውሰዋል። በዘንድሮው በጀት ዓመት የአንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ጭማሪ በማሳየት አራት ሚሊዮን ሄክታር አካባቢ ማድረስ ተችሏል ብለዋል።

የተመዘገበው ለውጥ በቂ አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፣ ከዚህም በላይ ፈጥኖ እንዲሄድና የተሻለ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቃል ብለዋል። ለተመዘገበው ውጤትም ከአመራሩ እስከ አርሶና አርብቶ አደሩ ድረስ የጋራ ግንዛቤ ፈጥሮ ወደ ሥራ መግባቱ አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአጠቃላይ የ2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት የታየበት መሆኑን ዶክተር ግርማ አስረድተዋል። በአሁኑ ወቅት የሰብል እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ ትኩረት እንደሚፈልግ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል። በዘር የተሸፈነው 17 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት አዝመራ እስኪደርስና እስኪሰበሰብ ድረስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባም አስገንዝበዋል። የአረም ቁጥጥርና ክትትል ሥራው እንዲጠናከር እንዲሁም በምርት አሰባሰብ ወቅት የምርት ብክነቶች እንዳይፈጠሩ መሥራት የግድ እንደሆነ አመላክተዋል።




**በመኸር ወቅት 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል፤ በእዚህም እቅዱ ሙሉ ለሙሉ ተሳክቷል። በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታሩ በክላስተር ወይም በኩታ ገጠም እርሻ የተሸፈነ ነው**

በተለይም ድንበር ዘለል ሰብል አጥፊ እንደ በረሃ አንበጣ እና ግሪሳ ወፍ የመሳሰሉትን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራው በባህላዊ መንገድ እንዲሁም በአውሮፕላን በታገዘ ርጭት እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በአሁኑ ወቅት የበረሃ አንበጣን ሙሉ ለሙሉ በመከላከል በቁጥጥር ሥር ማዋል እንደተቻለ ነው የተናገሩት።

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ ይህ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ በቀጣይነትም መሠራት ይኖርበታል። የበረሃ አንበጣው ከሀገር ውስጥ ብቻ የሚነሳ ባለመሆኑና ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ጭምር የሚነሳ በመሆኑ ከክልሎች ጋር በሚደረግ ጠንካራ የቅንጅት ሥራ ወደ መሀል ሀገር እንዳይመጣ የመቆጣጠርና የመከላከል ሥራ ተሰርቷል። ይህም ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የበረሃ አንበጣ ክስተቱ የተወሰኑ ክልሎችን መነካካቱን ገልጸው፣ እነሱም አፋር፣ ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ድሬዳዋና ሶማሌ አጎራባች የሆኑ ክልሎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ የግብርና ሚኒስቴር ክትትል ከሚያደርጋቸው ሰብል አጥፊዎች መካከል ግሪሳ ወፍ አንዱ ነው። ግሪሳ ወፍ እንደ ወፍ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝና የብዝሃ ሕይወት አንድ አካል መሆኑ ይታወቃል። ይህ ወፍ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኝ ሲሆን፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ በብዛት ይገኛል። እነሱም በቀድሞው ደቡብ ክልል በአሁኑ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ ዞንና ጉራጌ ዞን አካባቢዎች፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ በአርሲ ዝዋይ ዱግዳ፣ እንዲሁም በአማራ ክልል ሸዋሮቢትና ደቡብ ወሎ አካባቢዎች ግሪሳ ወፍ በብዛት ይገኛል። ወደ ምስራቅ አካባቢም እንዲሁ ባቢሌና በሶማሌ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች በስፋት ይታያል፡፡

የግሪሳ ወፍ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመከላከል ሥራ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ በእነዚሁ አካባቢዎች ማለትም በአማራ ክልል፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎችና ባቢሌ አካባቢ የመጀመሪያው ዙር ርጭት እየተካሄደ መሆኑን አስታውቀዋል። በአማራ ክልል ሁለተኛው ዙር ርጭት እንደሚካሄድ ጠቅሰው፣ የግሪሳ ወፍን የመቆጣጠርና የመከላከል ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡

ሚኒስትሩ ግሪሳ ወፍ ባለባቸው አካባቢዎች ሁሉ ርጭት እንደማይደረግ አስታውቀው፣ በቅድሚያ ባለሙያዎች በሚያደርጉት ጥናት መሠረት የግሪሳ ወፍ ስበስቡ አስጊ መሆን ተረጋግጦ ጥናቱ በሚኖረው ውጤት መሠረት እንደሚረጭ አስረድተዋል። ከአቅም በላይና ከመጠን ያለፈ ካልሆነ በስተቀር በአርሶ አደሩ አቅም በባህላዊ መንገድ የመከላከል ሥራው እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡

መደበኛው የሰብል እንክብካቤ የማረምና የእጽዋት ጥበቃ ሥራ በክልል ደረጃ ተጠናክሮ መቀጠሉንም ሚኒስትሩ አመልክተዋል። በአሁኑ ወቅት ያለው የመኸር ሁኔታ አበረታች ውጤት የታየበት እንደሆነም ገልጸው፣ የተሻለ የሰብል ግምገማ እንዳለም ከመስክ ጉብኝት መረዳት መቻሉን ተናግረዋል። ይህን ውጤታማነት ለማስቀጠል ምርቱ ተሰብስቦ እስኪጠቃለል ድረስ ተከታታይ የሆነ ክትትል ማድረግ እንደሚገባም አስታውቀዋል፡፡

በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተለይም በሰሜን በተወሰነ መጠን፣ በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች የዝናብ መቆራረጥ፣ የመጠን መቀነስና እጥረት ስለሚያስከትለው ተጽዕኖ የግብርና ሚኒስቴር የሚደርሱት ሪፖርቶች እንዳሉ ገልጸው፤ ይህንንም ከግንዛቤ ውስጥ መግባቱን ተናግረዋል። በዚህ ላይ ከክልሎች ጋር በመወያየትና በመተባበር ችግሩ ምን ያህል ሊሰፋ ይችላል የሚለውን ለማወቅና ለመከላከል ከወዲሁ የዳሰሳ ጥናት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስትሩ በአሁኑ ወቅት ጥናቱ የተሟላ ባይሆንም በቀጣይነት ችግሩን መከላከል ይጠቅማል ሲሉ ገልጸው፣ በተለይም ከአደጋና ስጋት መከላከል ጋር በመሆን ከዝናብ መቆራረጥና እጥረት አንጻር ሙሉ ለሙሉ ከምርት ውጭ ሊሆኑ የሚችሉ አካባቢዎች ካሉ የመለየትና የመደገፍ ሥራ ይሰራል ብለዋል። ከዚህ አንጻር ከተሠሩ ሥራዎች መካከል አንዱ የመስኖ ሥራ እንደሆነ ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅትም ከመኸር እርሻ ሥራ ጎን ለጎን የመስኖ ሥራን ለመሥራት የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ የመስኖ ሥራ ሁለት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች አሉት። ስንዴን በበጋ መስኖ የማልማቱ ሥራ እየሰፋና እየተለመደ በመምጣቱ አንደኛውና ዋናው ጥቅሙ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በተለይም ዝናብ በተቆራረጠባቸው አካባቢዎች ያለውን የመስኖ አማራጭ በመጠቀም በፍጥነት ወደ ማምረት ሥራ ለመግባት የሚያስችል መሆኑ ነው። ከሁሉም ክልሎች ጋር በተደረገው የዝግጅት ምዕራፍ ግምገማም የበጋ መስኖ ልማት የተሻለ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

ለአብነትም በዘንድሮው በጀት ዓመት ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ እንደሚሸፈን ከክልሎች ጋር መግባባት ላይ ተደርሷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ባለፈው በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ የተሠራው አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሆኑን ገልጸዋል። በዘንድሮው በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴን ከእጥፍ በላይ ለማልማት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# እንደወርቅ ተፈትነው ውጤት ያመጡ ኮከቦች

ገርማ መንግሥቱ

የሰሞኑ አነጋጋሪ ርዕሰ ጉዳይ ምን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ጉዳዩ ከመታወቅ ባለፈ ሁሉ የሚያወራው ሆኗል፡፡ አዎ! የዘንድሮው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤት እጅግ አስደንጋጭ ሆኖ አልፏል፡፡ መቼም ውድቀት ሲኖር ሁሉም ጆሮውን ሰጥቶ ያዳምጣል፡፡ ሁሉም ይተቻል፡፡ ሁሉም ስለውድቀቱ አብዝቶ ያወራል፡፡ ከሰሞኑ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ አብዛኛው ሰው ሲያወራ የነበረው ስለተመዘገበው አስከፊ ውጤትና ስለወደቁ ተማሪዎች ብዛት እንጂ ስላለፉት ተማሪዎች አልነበረም፡፡

ምንጊዜም ቢሆን ፈተና ሁለት ተቃራኒ ውጤቶችን እንደሚያስተናግድ ይታወቃል። ይህን ደግሞ በትምህርት ዓለም ውስጥ ያለፈ ሁሉ አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ ጉዳዩም በዚህ መስመር ላለፉና ለብዙዎች አዲስ አይደለም፡፡ በትምህርት ዓለም መውደቅና ማለፍ የተለመዱ ጉዳዮች እንደሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ታዲያ ለየት የሚያደርጋቸው ዐብይ ጉዳይ ግን አለ። ሁለቱን ለየት የሚያደርጋቸው በየትኛውም የፈተና ውጤት የአላፊው ቁጥር ሲበዛ የሚወድቀው ቁጥር አነስተኛና፣ ምናልባትም ከአጠቃላይ ተፈታኞች ቁጥር አንፃር ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል እንኳን አለመሆኑ ነው። የዘንድሮው ግን በእጅጉ ይለያል።

የዘንድሮውን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና አስመልክቶ የትምህርት ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ በአጠቃላይ በ2015 ዓ.ም ከተፈተኑ ተማሪዎች ውስጥ 3 ነጥብ 2 በመቶ ብቻ 50 በመቶ እና ከዛ በላይ ማስመዝገባቸውን አስታውቋል፡፡ ይህም ውጤት ከአምናው የተሻለ የፈተና ቁጥጥር ሥርዓት በሚገባ መዘርጋቱን ያመላክታል፡፡ በተፈጥሮ ሳይንስና በማህበራዊ ሳይንስ ለፈተና ከተቀመጡ በድምሩ 845 ሺህ 677 ተማሪዎች 50 ከመቶና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡት 31ሺህ 224 ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውም በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡ 160ሺህ የሚሆኑ ተማሪዎችን በሬሜዲያል ፕሮግራም ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚቀበሉም ተጠቁሟል፡፡

በዚሁ መግለጫ መሠረት አምና 13 ሺህ 600 ተማሪዎች ፈተና አቋርጠው የውጡ ሲሆን ዘንድሮ ምንም ተማሪ አላቋርጠም። በአማካኝ 28 ነጥብ 65 በመቶ በአንድ ተማሪ፤ በተፈጥሮ ሳይንስ 29 ነጥብ 8 በመቶ፤ በማህበራዊ ሳይንስ 27 በመቶ፤ በግል ፈተና የወሰዱ ከ160 ሺህ በላይ ተፈታኞች 14 ሺህ፤ በኢትዮጵያ ከፍተኛው 649 በተፈጥሮ ሳይንስ (ሴት ተማሪ) ከክሩዝ ትምህርት ቤት፤ ከማህበራዊ ሳይንስ 533 ከደብረ ማርቆስ አዳሪ ትምህርት ቤት፤ ከ600 በላይ ያመጡ 205 ተማሪዎች ከተፈጥሮ ሳይንስ፤ ከማህበራዊ ሳይንስ 15 ተማሪዎች ከ500 በላይ ከ600፤ ከ50 ከመቶ በላይ ተማሪዎች ከ26 ከመቶ በታች አምጥተዋል፡፡

ምንም እንኳን የዘንድሮው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ውጤት አስደንጋጭ ቢሆንም፣ በዚህ መካከል እንደ ወርቅ ተፈትነው ነጥረው በመውጣት ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችሉ ኮከብ ተማሪዎች ተከስተዋል። እነዚህ ኮከቦች ከፈለቁባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው አንጋፋው የቀዳማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ይገኝበታል፡፡ ትምህርት ቤቱ እንደ ሌሎች አቻዎቹ ብዛት ያላቸው የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን አስፈትኗል፡፡ የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም የተወሰኑ ተማሪዎቹን ለውጤት አብቅቷል። ከዚህ ትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ ታዲያ አንዱ ተማሪ አበራ ሁሉፍ ነው፡፡

ተማሪ አበራ ሁሉፍ ተወልዶ ያደገው ትግራይ ክልል መቐሌ ከተማ ነው። አስፈላጊ ያልሆነውና የበርካታ ንፁሃንን ሕይወት የቀጠፈው ጦርነት መጥቶ ትምህርቱን እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ እዛው ነበር። እዛው ቆየ እንጂ አቋርጦም ወደየትም አልሄደም። ከሶስት ዓመት ቆይታ በኋላ ግን በቤተሰቦቹ አማካኝነት ያቋረጠውን ትምህርቱን ይቀጥል ዘንድ ወደ ሀገሪቱ መዲና አዲስ አበባ መጣ።



ተማሪ አበራ ሁሉፍ፣



ወይዘሮ ዘላለም ሲሳይ፣

ተማሪ አበራ ሁሉፍ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ የትምህርት ቤቶች መከፈቻ ጊዜ ሳይሆን የመጀመሪያው መንፈቀ-ዓመት ተጠናቅቆ ተማሪዎች ሁለተኛውን መንፈቀ-ዓመት ለመጀመር በዝግጅት ላይ በነበሩበት ወቅት ነበር። የተማሪ አበራ ቤተሰቦች ትምህርቱን ከሁለተኛው ሴሚስተር እንዲቀጥልላቸው በማሰብ ትምህርት ቤት ማፈላለጉን ተያያዙት። ተሳካላቸውና ለአበራ በምኒልክ 2ኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት ቦታ ተገኘለት። ከዛም ትምህርቱንም ቀጠለ።

የ12ኛ ክፍል ትምህርት ሄዶ ሄዶ ያው ማጠቃለያው በመላ ሀገሪቱ የሚሰጠው መልቀቂያ ፈተና ነውና ለፈተና ተቀመጠ። በሚገርም ሁኔታም፣ በመርፌ ቀዳዳ እንደ መሹለክ በሚቆጠረው የዘንድሮ ፈተና ውጤታማ ብቻ ሳይሆን በጥሩ ውጤት ማለፍ ቻለ፡፡

ተማሪ አበራ ‹‹የመቐሌ ልጅ ነኝ›› ይላል ንግግሩን ሲጀምር፡፡ ትምህርቴን ስከታተል የነበረው እዛው መቐሌ የሚገኝ፣ ‹‹ቀለሚ›› የሚባል ትምህርት ቤት ውስጥ ነበር። ነገር ግን ጦርነቱ መጥቶ ከትምህርቴ ለየኝ፤ አቋረጥኩ። ለሶስት ዓመታትም በስጋትና አእምሮ መረበሽ ውስጥ ነው የቆየሁት። ከዛ ቤተሰቦቼ ይዘውኝ ወደ አዲስ አበባ መጡ። ቦታ ፈለጉና ትምህርት ቤት አስገቡኝ። ትምህርት ቤት የገባሁት ፈተናው አንድ ወር ሲቀረው ነበር፡፡ ምንም ማድረግ አልቻልኩም፡፡ ፈተናው ሲደርስ ለፈተና ተቀመጥኩ። ያው አለፍኩ።

‹‹ፈተናው ጥሩ ነው። በጣም ቀላል ነበር። ትንሽ ላጠና ተማሪ ያን ያህል ከባድ የሚባል አልበረም›› ሲል ይናገራል ተማሪ አበራ፡፡ ተማሪዎች በብዛት በፈተናው ሊወድቁ የቻሉት ያን ያህል ፈተናው ከባድ ሆኖ ተማሪው ሳይሆን ኩረጃን መጠበቁና አለማጥናቱ ነው ይላል፡፡ ተማሪው መኮራረጅን ባይጠብቅ፣ ቢያጠናና ቢዘጋጅ ኖሮ አብዛኛው ተፈታኝ ሊያልፍ ይችል እንደነበርም ያመለክታል፡፡

‹‹እንደ ፈተናው ቅለት እኔ ራሴ 555 ማምጣቴ በጣም አናድዶኛል›› ሲል ተማሪ አበራ በቁጭት ይናገራል፡፡ ከዚህ በላይ ማምጣት ነበረብኝ። ግን ይሁን፤ በሁለትና ሶስት ወር ዝግጅት ስለሆነ ይህንን ውጤት ማምጣቴም ምንም አይደለም ሲል ይገልፃል፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በተለይ ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ኮምፒውተር ሳይንስ ማጥናት እንደሚፈልግ ይጠቁማል፡፡ ለወደፊቱ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ከተፈለገ የመምህራን ድጋፍ በጣም አስፈላጊ መሆኑንም ይጠቅሳል፡፡ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት እንዳለባቸውም ያመለክታል፡፡ በትርፍ ሰዓትም ጭምር ለተማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግና ይህ ከተደረገ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት የማያመጡበት ሰፊ እድል እንደሚኖር ይገልፃል፡፡

**ምንጊዜም ቢሆን ፈተና ሁለት ተቃራኒ ውጤቶችን እንደሚያስተናግድ ይታወቃል። ይህን ደግሞ በትምህርት ዓለም ውስጥ ያለፈ ሁሉ አሳምሮ ያውቀዋል፡፡ ጉዳዩም በዚህ መስመር ላለፉና ለብዙዎች አዲስ አይደለም**

‹‹ቤተሰቦቼ ማለፌን ሲሰሙ ማመን ነው ያቃታቸው›› የሚለው ተማሪ አበራ፤ ከሶስት ዓመት በላይ ትምህርቴን አቋርጬ፣ ጦርነት በሚካሄድበት ከተማ ውስጥ ቆይቼ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሶስት በመቶ ብቻ ተማሪ ነው ያለፈው ሲባል እኔን ያልፋል ብለው አልጠበቁም ነበር›› ሲል ያስረዳል፡፡ ውጤቴን ሲሰሙ ከሚገባው በላይ ነው የተደሰቱት ይላል፡፡

ባለፈው ዓመት 100 በመቶ በማሳለፍ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ውጤትም በሀገር አቀፍ ደረጃ አንደኛ ወጥቶ የነበረውና ዘንድሮ ደግሞ 75 ተማሪዎችን አስፈትኖ 72ቱን ያሳለፈው ሌላኛው ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ኮከቦች መፍለቂያ ሆኗል፡፡

ወይዘሮ ዘላለም ሲሳይ የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ቀዳማዊ ምኒልክ ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ ርዕሰ መምህር ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚናገሩት የካምፓሱ ተማሪዎች አይደለም በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ናቸው። ዘንድሮ ሶስት ተማሪዎች ከ350 በታች በማምጣት በተለያዩ ምክንያቶች ማለፍ ያልቻሉ ቢሆኑም አምስት ተማሪዎች ከ600 በላይ ውጤት ማምጣት ችለዋል፡፡

ለአምስተኛ ጊዜ ያስፈተነው ይህ ተቋም በሚቀጥለው ዓመት ስድስተኛ ዙር የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስፈትን ሲሆን፣ እነዚህ ተፈታኞች ሙሉ ለሙሉ መቶ ከመቶ የሚያልፉ ናቸው። ለዚህ መነሻ የሆነውም እስካሁን የተመዘገበው መልካም ውጤት ነው፡፡

ተማሪዎች ይህን ጥሩ ውጤት ማምጣት የቻሉት በክፍል ከ25 እስከ 30 ተማሪዎች ብቻ እንዲማሩ በመደረጉ፣ በዩኒቨርሲቲ መምህራን ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመማራቸው ፣ ወላጆች ከትምህርት ቤቱ ጋር በቅርበትና በመደጋገፍ በመሥራታቸው፤ ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የሚያዘጋጃቸው ጠንከር ያሉ ሞዴል ፈተናዎች መሰጠታቸውና ሙሉ ዝግጅት መኖሩ እንዲሁም የራሳቸው የተማሪዎች የእርስ በእርስ መደጋገፍ መኖሩ ነው፡፡

ርዕሰ መምህሯ እንደሚገልፁት እርሳቸው የሚመሩት ተቋም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በከተማዋ ዙሪያ የ8ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ፤ ለተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ዝንባሌና የፈጠራ ተሰጥኦ ያላቸው፣ 10ኛ ክፍልን ካጠናቀቁ በኋላ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ ብቻ መቀጠል ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ይቀበላል። በተግባር የተደገፈ ትምህርት በመስጠት የላቁ ተመራማሪዎችን ማፍራት ደግሞ ተቀዳሚው አላማ ነው፡፡ የወደፊት እቅዱም ከመዋእለ ሕፃናት (ኬጂ) ጀምሮ፣ ከሀገርም አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሞዴል ተማሪዎችን ማፍራት ላይ መሥራት ይሆናል፡፡

የዘንድሮውን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን በሚመለከት የተቋሙ ተማሪዎች በማለፋቸው ደስ ሊያሰኝ ይችላል፡፡ እንደ ሀገር ግን ጉዳዩ ያስፈራል፣ ያሳፍራልም። ያለፉ ተማሪዎች ላይ የተቋሙ ዐሻራ እንዳለበት ሁሉ የወደቁ ተማሪዎች ላይም የተቋሙ ዐሻራ አለበት። ተማሪዎች በዚህ ደረጃ ወደቁ ማለት እንደ ሀገርም ውድቀትና ጉዳት ነው። ሄዶ ሄዶ በአንድ ወቅት ሀገር በሁሉም ዘርፍ ባለሙያዎችን ስትፈልግ ልታጣ ሁሉ ስለምትችል ጉዳቱ በዚህ ልክ ነው መታየት ያለበት። በዚህ ደረጃ፣ ትንሽ ቁጥር ያለውን ተማሪ ይዞ መሄዱም የትም ድረስ አያዋጣም። ይህ በጥልቅ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል እየተጠና ያለ ጥናት አለ፡፡ እሱ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በማንኛውም ጉዳይ የትምህርት ባለ ድርሻ አካላትን የግድ ማሳተፍ ያስፈልጋል። መነጋገር ያስፈልጋል። መንግሥት የመምህራንን ኑሮም ማየት አለበት። መምህራን መኖር በሚችሉበት ደረጃ ሊኖሩ ይገባል። ዞሮ ዞሮ ተማሪ በአንድ ቀን ፈተና የመጨረሻ ማንነቱ አይለካም። ፈተና አንዱ የእውቀት መለኪያ እንጂ የሁሉም እውቀት መለኪያ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም አላለፉም በተባሉት በኩል ምንም የሚረብሽ ሁኔታ መኖር የለበትም።

የመማሪያ መጻሕፍት እጥረትን በተመለከተም “ለእኛ በፒዲኤፍ ደርሶን ለልጆቻችን አዳርሰናል። ይህ ለእኛ ልጆች ችግር ላይሆን ይችላል። እዛ፣ እሩቅ ላለው ግን እንደዚህ ቀላል ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ባለሀብቱንም፣ ባለ ድርሻ አካላትንም አስተባብሮ የመማሪያ መጻሕፍት ለተማሪዎች የሚደርሱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል›› ሲሉም ነው ርዕሰ መመምህሯ ያመለከቱት፡፡

# ‹‹የወደብና የባህር በር ጉዳይ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ያለ ነው››

**አማረ ቀናው(ዶ/ር)**

**በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት መሪ ተመራማሪ**

አስቴር ኤልያስ

**ዶክተር አማረ ቀናው በውጭ ጉዳይ ኢንስትቲዩት መሪ ተመራማሪና የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር ጀነራል ናቸው። ዶክተሩ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደህንነት ጥናት ረዳት ፕሮፌሰርና የምርምር ጉዳዮች ዳይሬክተር ሆነውም አገልግለዋል። ከዘመናዊው ዓለም አቀፍ ደህንነት ክልላዊ ውህደትና ከዓለም አቀፍ ትብብር ጋር በተያያዙ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ በርካታ ጽሑፎችንም ለማሳተም ችለዋል።**

**አዲስ ዘመን ከእኚህ መሪ ተመራማሪ ጋር በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና እና መካከለኛው ምስራቅ ላይ ያተኮረ እንዲሁም ኢትዮጵያ በባህር በር ጉዳይ ላይ መነጋገር አለባት በሚል የሰሞኑን ዋና አጀንዳ በሆነው ቀይ ባህር ላይ አስመልክቶ ከእርሳቸው ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የምትገኝበትን የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና አሁን ካለው ዓለም አቀፍ ፖለቲካ አንጻር እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር አማረ፡-** በብዙ መልኩ ምስራቅ አፍሪካ በተለይም ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ የምንለውን አካባቢ አሁን ካለው የጂኦፖለቲካ ሽኩታ አንጻር በተለየ መንገድ ሊታይ ይችላል። አካባቢው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ በኋላ ላይም በቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን ከፍተኛ የሆነ የኃያላን ፉክክር የሚታይበት መድረክ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ደግሞ እኤአ ከ1990ዎቹ ወዲህ ከዚህ ዓይነት ሁኔታ በተወሰነ መልኩም ቢሆን መውጣት የታየበት አዝማሚያ ነበር። ይሁንና በቅርቡ ደግሞ በቀጣናው አካባቢ የመፎካከሩ ነገር ተመልሶ መጥቷል።

ፉክክሩ የኃያላን ብቻ ሳይሆን በቀጣናው አካባቢ አዳዲስ ኃያላን ሀገራት የተፈጠሩበት ሁኔታም እየታየ ነው። ለአብነት ያህል እነዚህ አዳዲስ የተባሉ ሀገራት ከአረቡ ሀገራት እነሳዑዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች፣ ቱርክ፣ ኢራን እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ ወደኃያላኑ ተርታ የመሰለፍ አዝማሚያ የታየባቸው ናቸው ማለት ይቻላል።

ከዚሁ ከኃያላን ፉክክር ጋር ተያይዞ እንደሚታወሰው በምስራቅ አፍሪካ ወይም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚገኙ ሀገራት በአብዛኛው በውክልና ጦርነት ውስጥ ገብተው እንደነበር ይታወቃል። አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በቀጣናው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቀዝቀዝ ብሎ የነበረው ሁኔታ መልሶ ማንሰራራት ታይቶበታል። ይህ እንቅስቃሴ ደግሞ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለቀጣናው ሀገራት የደህንነት ስጋት ሊሆን እንደሚችል ይስተዋላል። ከዚህም የተነሳ ምናልባትም ቀጣናው ተመልሶ የውክልና ጦርነት ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰትበት ይችላል።

ሌላው፣ አካባቢው የመልክዓ ምድራዊ ፖለቲካ ጠቀሜታው እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው። የምናውቃቸው የአውሮፓ፣ የኤዥያ፣ የአፍሪካ፣ አውስትራሊያንም ጨምሮ የተለያዩ ክፍለ ዓለማትን በማገናኘት እንደ መገናኛ መስመር ተደርጎ የሚቆጠር ነው። ስለዚህ ኃያላን ሀገራት አካባቢውን ለመቆጣጠር ትልቅ ሹክቻ ውስጥ ናቸው ማለት ይቻላል። ይህ አሁንም እንደገና እየተጠናከረ ነው።

ከዚያ ጋር ተያይዞ የኃያላኑ ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያ እንዲሁም የቀጣናው ኃያላን ጭምር በአካባቢው ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያ መፍጠራቸው እንዲሁም አካባቢውን ለመቆጣጠር የሚያደርጉት ሽኩቻ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል።

እንደሚታወቀው በተለያየ ጊዜ በአካባቢው ግጭቶች ያገረሻሉ። በተለይም በሀገራቱ መካከል በድንበር ጉዳይም ሆነ ማንነትን መሠረት ባደረገ ምክንያት ግጭቶች ሲከሰቱ የነበረበት አካባቢ ነው። ይሁንና አስቀድሜ እንደገለጽኩት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ረግበው ነበር።

ይሁንና ከኃያላኑ ፉክክር ጋር ተያይዞ እንደገና የማገርሸትና ወደግጭት የመምጣት ሁኔታ እየታየበት ያለ ቀጣና እየሆነ ነው። በተጨማሪም በተወሰነ መልኩም ቢሆን ድንበር ዘለል የምንላቸው የደህንነት ስጋቶች አሉ። እነዚህም የተለያዩ የዝውውር ዓይነቶች ሲሆኑ፣ በተለይ የመድኃኒት ዝውውር፣ የሰው ዝውውር ብሎም የመሳሪያ ዝውውር የሚደረግበት አካባቢ በመሆን ላይ ነው።

ስለዚህ በአካባቢው የሰፈረው አብዛኛው ማኅበረሰብ ተመሳሳይ ማንነት ያለው ዓይነት በመሆኑ በአብዛኛው ለእንደዚህ ዓይነት ዝውውሮች የተጋለጠ ነው። ይህ ደግሞ ለቀጣናው ሀገራት የደህንነት ስጋት እየሆነ መጥቷል። ከዚያ ጋር ተያይዞ የኃያላን ጎራ መደበላለቅ አለ። ሀገራቱ ደግሞ "ከየትኛው ኃያል ጀርባ መሰለፍ አለብኝ" የሚል ስጋት በየጊዜ እየተደቀነባቸው ነውና ራሳቸውን በየትኛው መስመር ማግኘት እንዳለባቸው የሚሻኮቱበት ሁኔታም የሚታይበት ነው።

ሌላኛው አካባቢው ከድንበር ዘለል ጦርነቶች ይልቅ በውስጣዊ ጦርነቶች የመጠመድ ሁኔታ እየተንጸባረቀበት ነው። በአንድ ወቅት አካባቢው ይካሄድበት የነበረው ድንበር ዘለል የሆኑ ግጭቶች ነው። ይህ ግን በተወሰነ መልኩም ቢሆን እየረገበ የመጣ ቢሆንም አሁን ደግሞ በውስጥ ጉዳይ የመጠመድ ሁኔታ ይስተዋላል።

ለአብነት ያህል የቅርቡን የሱዳንን የውስጥ ግጭት መውሰድ እንችላለን። ሀገራችን ኢትዮጵያም በተወሰነ መልኩ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት የውስጥ ግጭቶች የነበረብን እንደሆነ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በመሆኑም የውስጥ ግጭቶቹ የዚህ አካባቢ ጂኦፖለቲካ ባህሪ ሆኖ ጎልቶ እየወጣ ነው። ሀገራቱ በራሳቸው የውስጥ ጉዳይ የመጠመዳቸው ሁኔታ ለአካባቢው የደህንነት ስጋት ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

ምክንያቱም ሱዳን ላይ የሚካሄድ ግጭት እኛም ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። እኛም ዘንድ የሚካሄድ ግጭት ደግሞ ምናልባት ኬንያ፣ ጂቡቲ እንዲሁም ኤርትራ ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አዳዲስ የሆኑ የደህንነት ስጋቶች እንደገና በአዲስ መልክ እየመጡ ያሉ ናቸው ማለት ይቻላል። ምንም እንኳን ቀጣናውን የቀድሞዎቹ ስጋቶች ሙሉ ለሙሉ ለቀውታል ብሎ ለመናገር ባያስደፍርም አዳዲስ ስጋቶች የጂኦፖለቲካ ባህሪ መገለጫ ሆነዋል ማለት ይቻላል።

ሌላኛው በቀጣናው ባሉ ሀገራት የተካሄደው የመንግሥት ለውጥ ነውጥ አልባ በሆነ መንገድ መሆኑ የማይካድ ነው። ዴሞክራሲያዊ ነበር ብሎ ለመፈረጅ ቢከብድም የተካሄዱ የመንግሥት ለውጦች በተወሰነ መልኩ ነውጥ አልባ ነበሩ ማለት ይቻላል። ለአብነት ያህል የሀገራችንን፣ የሱማሊያን በቅርቡ ደግሞ የኬንያን የመንግሥት ለውጦች ስንመለከት ሰላማዊ ነበሩ ማለት ይቻላል። ለውጦቹ በምርጫ የተካሄዱ ናቸው፤ ምናልባት ዴሞክራሲያዊነታቸው እንደየሀገሩ ባህሪ ሊለያይ ቢችልም ለውጦቹ ያለ ግጭት መካሄዳቸውና ሕዝባዊ በሆነ መንገድ የመጣ በመሆኑ አንድ ጥሩ የሚባል ባህሪ ነው ብለን መውሰድ እንችላለን።

ቀደም ሲል በድንበር ግጭት የሚታወቀው ይህ አካባቢ አሁን አሁን ግጭቶች ሲከሰቱም እንኳ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች እየበዙ የመጡበት ሆኗል። ከዚህም የተነሳ በቀጥታ ወደጦርነት የመግባቱ ነገር እየቀነሰ ይገኛል። እንደ ምሳሌ መጥቀስ የምንችለው የኢትዮጵያንና የሱዳንን በቅርብ የነበረው የድንበር ግጭትን ሲሆን፣ ይህን በአርዓያነት ልንወስደው እንችላለን።

በወቅቱ በተፈጠረ ክፍተት የሱዳን ኃይል በተወሰነ መልኩም ቢሆን የኢትዮጵያን መሬት ተቆጣጥሮ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ስለሆነም በሁለቱ ሀገራት መካከል የዲፕሎማሲ መሻከር ሊፈጥር ይችላል የሚል ሃሳብም ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ችግሮችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ጥረት አድርጓል። እስካሁንም ቢሆን ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተፈቷል ባይባልም በቀጥታ ግን ወደ ጦርነት አልተገባምና ችግሮችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ባህሪ እየመጣ ነው ማለት ያስችላል።

በሌላ መንገድ ግን የእኛንም ጨምሮ በብዙ



ፎቶ፡ በገባቦ ገብሬ

የአካባቢው ወይም የቀጣናው ሀገራት ታጣቂነት የምንለው ስሜት እጅግ እየተባባሰ መጥቷል ማለት ይቻላል። በእርግጥ እንደዓለም አቀፍም ሲታይ ከመደበኛ ይልቅ ወደ ኢ-መደበኛ ሁኔታ ውስጥ የመግባት ሁኔታ አዝማሚያ ተስተውሏል። ለምሳሌ በሀገራችን ያለው ሁኔታ ሲታይ ኢ-መደበኛ የሆኑ አካላት መደበኛ የሆነውን መንግሥት የሚፈትኑበት ሁኔታ እየተከሰተ ይገኛል።

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በጣም እየጎላ የመጣውና በአሁን ወቅት በተለይ የራሽያ እና የዩክሬን እንዲሁም የእስራኤል እና የሐማስ ጦርነት ቀጣናችንን ሊያናውጡት የሚችሉበት ሁኔታ የለም ማለት አይቻልም። ለዚህ ደግሞ ቀጣናዊ መፍትሔ ማፈላለግ ያስፈልጋል። በእርግጥ ለቀጣናዊ ችግሮች ቀጣናዊ የመፍትሔ አፈላለግ መርህ አለ፤ ምክንያት በአንድ ሀገር ብቻ ቀጣናዊ ሰላምንና ደህንነትን ማስከበር ከባድ ስለሆነ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደሚታወቀው ከሰሞኑ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ስለባህር በርና ስለ ቀይ ባህር ጉዳይ ገለጻ አድርገዋል። የተነሳው ርዕስ ወቅታዊ ነው ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር አማረ፡-** ወቅታዊ ነው ብሎ ለመፈረጅ ብዙ ነገር መጥቀስ ያስፈልጋል። አንድ ሀገር የባህር በር እንደሚያስፈልገው ይታወቃል። የባህር በር ለኢኮኖሚ እድገት፣ ለብሔራዊ ጥቅም እንዲሁም ለደህንነትም ጭምር አስፈላጊ እንደመሆኑ እነዚህን ለማስጠበቅ የምንጠቀምበት አንዱ መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል።

የባህር በር ማግኘት የሚባለው ነገር በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል። አንደኛው ሙሉ በሙሉ ከባህር ጋር የሚያገናኘው ወደብ በባለቤትነት ወይም የራስ የሆነ መሬት ማግኘት ነው። ሁለተኛው ደግሞ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ የባህር በር ተጠቅሞ የአንድን ሀገር ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ናቸው።

ከሁለቱም አንጻር ስለጉዳዩ መነጋገር ያስፈልጋል። እንደሚታወቀው እኛ የራሳችን የሆነ ወደብ የለንም። እየተገለገልን ያለነው የሌሎችን ወደብ ተከራይተን ነው። ስለዚህ ጥያቄው ቀድሞም ቢሆን በውስጣችን ያለ ነው። በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ያለ ነው። የማይመለስ ከሆነም የሚቀጥል ነው።

የባህር በር የአንድን ሀገር ብሔራዊ ጥቅም ሊያስጠብቁ ከሚችሉ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ እንደመሆኑ ርዕሰ ጉዳዩ መቼም ቢሆን ሊነሳ የሚችል ነው። ጉዳዩን መንግሥት በሚፈልገው ሰዓት ብቻ ስላነሳው አይደለም፤ እንደእነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ዞሮ ዞሮ በሕዝብም የሚነሱ ናቸው። ስለዚህም የባህር በር ጥያቄ መጠየቅ ያለበት በዚህና በዚያኛው ጊዜ ይባላል ብዬ አላስብም። ጊዜም ይገደብለታል ብዬ አልልም። ጥያቄው በየትኛውም ጊዜ ሊነሳ የሚችል ሲሆን፣ ሊለያይ የሚችለው እንዴት ተደርጎ ነው ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው የሚለው ነው።

የቀይ ባህርን ሁኔታ እግረ መንገድሽን ካነሳሽው አይቀር በቅርቡ አንድ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም በሸራተን አዲስ ሆቴል በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት አስተባባሪነት ተካሂዶ ነበር። ታዳሚዎቹ ከ200 በላይ የሚሆኑ የመንግሥት አማካሪዎች (ቲንክ ታንክ) ሲሆኑ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከአፍሪካ ቀንድና ከመካከለኛው ምስራቅ ማለትም ከእስራኤልና ከአረብ ሀገራት የተውጣጡ ናቸው።

የኮንፈረንሱ ርዕስ ‹‹የቀይ ባህር የደህንነት ሁኔታ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹የወደብና የባህር በር...

ከ ገጽ 9 የዞረ

ቀጣናዊ ምክክርና ትብብር መልከዓ ፖለቲካዊ መጠላለፍ በበዛበት ዓለም ወቅት›› የሚል ነበር። ኮንፈረንሱን ስናዘጋጅ በመጀመሪያ ጽንሰ ሐሳብ ቀርጸን ነው። በቀይ ባህር አካባቢ ይካተታሉ ያልናቸውን በሙሉ አማክረንና ሃሳቡን ልከን ተሳታፊ እንዲሆኑ የተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኮንፈረንሱ ምን ያህል ጥናታዊ ጽሑፎች ቀረቡ? የተዘጋጀበት ዋና ዓላማስ ምን ነበር?**

**ዶክተር አማረ፡-** ወደ 20 ጥናቶች ሲሆኑ፤ ጥናቱን ያቀረቡት ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ በቀጣናው ካሉት ውስጥ ናቸው፤ ርዕሰ ጉዳዩ የቀይ ባህር የደህንነት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያጠነጠነ ነው። ወቅታዊ ሁኔታውን ካየን በኋላ ደግሞ ቀጣናዊ ትብብር የቀይ ባህርን ደህንነት ለማስጠበቅ ያስፈልጋል። ስለዚህ ኮንፈረንሱን ያዘጋጀነው ቀጣናዊ ትብብርንና ቀጣናዊ ምክክርን ለማጎልበት በማሰብ ነው።

ኮንፈረንሱን ስናዘጋጅ ሶስት ዓላማዎች ነበሩን። የመጀመሪያው ዓላማ በቀይ ባህር አካባቢ እስካሁን ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው? እስካሁን የነበሩት የደህንነት ስጋቶችስ የትኞቹ ናቸው? በአሁን ወቅት ደግሞ እየገዘፉ ያሉ የደህንነት ስጋቶች ምንድን ናቸው? ለቀጣዩ አምስትና አስር ዓመታትስ የደህንነት አደጋዎቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ነበር።

ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የቀይ ባህር የደህንነት ሁኔታን ለመከታተል ዲዛይን የሚደረጉ መድረኮች ወይም ፎረሞች ለምሳሌ አሁን እኛ የሌለንበት የቀይ ባህር ፎረም (Red sea forum) እንደሚባለው አሊያም ደግሞ የቀይ ባህር ጥምረት (Red sea Alliaince) ወይም ደግሞ የጂቡቲ የሥነ ምግባር ደንብ (Code of conduct) እንደሚባለው ዓይነት አደረጃጀቶች አሉ። ስለዚህ እነዚህና መሰል አደረጃጀቶች የአካባቢውን ደህንነት ለማስጠበቅ ምን ያህል ውጤታማ ናቸው? ውጤታማ ካልሆኑ ደግሞ ለወደፊቱ እንዴት አድርገን እነዚህን ማዕቀፎች እንቅረጻቸው? የሚለው ነበር በሁለተኛ ዓላማነት የተነሳው።

ሶስተኛው ዓላማ ደግሞ የቀጣናው ሀገራት የራሳቸው የሚያመሳስል ወይም አንድ የሚያደርግ ነገር ያላቸው ናቸው። ለምሳሌ በእምነት፣ በባህል እንዲሁም በማንነትም ጭምር አንድ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ። ስለዚህ አንድነታችንና የምንጋራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? የጋራ ተጠቃሚነታችንን ምን ያህል ሄደንበታል? የጋራ ተጠቃሚ የሚያደርጉን ነገሮችስ ምን ምን ነበሩ? እንዴትስ እየሰራንበት ነው በሚል ኮንፈረንሱ አካሄደናል።

በኮንፈረንሱ ከተነሱ ነገሮች ውስጥ እንደ ሀገር እኛም እንዲነሳና ውይይት እንዲደረግበት ካደረግነው ውስጥ አንዱ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት የነበሩ አደረጃጀቶች ምን ያህል ውጤታማ ነበሩ? የሚለው ጉዳይ ነው። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያንና እስራኤልን ያገለለ የቀይ ባህር ደህንነት ተለዋዋጭነት መድረክ (Red sea security dynamics forum) ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ለወደፊቱ እነዚህን መሰል ማዕቀፎች አካታች የሆነ መስፈርት ወጥቶላቸው በዛ መሠረት ትብብሩ መጠናከር እንዳለበት በኮንፈረንሱ የተሰመረበት ነበር።

ለምሳሌ ከዛ ውስጥ ከደህንነት ስጋት ውስጥ ከተነሱ ነገሮች ውስጥ አንዱ አንቺ እንዳነሳሽው የወደብ ጥያቄ ነበር። በእርግጥም እኛ ጉዳዩ ላይ ውይይት እንዲደረግበት እንፈልጋለን። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ወደብ ማግኘት ያለባት እንዴት ነው? እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ያለችው በጣም በቅርበት ነው። እናም ይህን ያህል ሕዝብ የያዘ ሀገር፣ ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታው በጣም የጎላ ሀገር በምስራቅ አፍሪካ የባህር በር ተጠቃሚ መሆን ይገባዋል። እንዲህም ሲባል የባህር በር ልናገኝ የምንችልበት ምን አማራጮች አሉ? የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው የሚለው ጉዳይ ተነስቶም ውይይት የተደረገበት መድረክ ነበር ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የታዳሚያኑ ግብረመልስ ምን ይመስል ነበር?**

**ዶክተር አማረ፡-** እንዲጋጣሚ ሆኖ ጠርተናቸው በግል ችግር ምክንያት ያልመጡት ከኤርትራ እንዲሁም ከወቅታዊ ችግር ምክንያት ደግሞ ከሱዳን ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ተገኝተዋል ማለት ይቻላል። ከዛ ውጭ ግን የጠራናቸው ሁሉም መጥተዋል ማለት ይቻላል።

የቀይ ባህር የትብብር መድረክ ከመፈጠሩ በፊት የጂቡቲ የሥነ ምግባር ደንብ አለ። ይህ ተመሳሳይ ዓላማ ያለው ማዕቀፍ ነበር። ይህ ማዕቀፍ በምስራቅ አፍሪካ እና በቀይ ባህር አካባቢ አጠቃላይ ያሉ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚያውክ፣ ሽብርተኛነትንና የባህር ላይ ውንብድናን



የሚከላከል ማዕከል ተደርጎ የተመሰረተው ኢኤአ 2009 ነው። እዛ ውስጥ ኢትዮጵያም አባል ነች።

የቀይ ባህር የደህንነት መድረክ ኢኤአ በሁለት ሺ አስራዎቹ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ ሆን ተብሎ አንዳንድ ሀገራት እንዳይካተቱ የተደነገገው ሊያስወጣቸው በሚችል መስፈርት ነው። ያልተካተቱትም ደግሞ ኢትዮጵያና እስራኤል ናቸው። መድረኩ ኢትዮጵያን ያካተተው የባህር በር የሌላት በሚል ሲሆን፤ እስራኤል ደግሞ ማንነቷ ከተቀረው ጋር አይመሳሰልም በሚል ነው። ይሁንና እንዲህ ዓይነቱ መስፈርት መቀመጥ አልነበረበትም። ለወደፊቱ አካታች የሆነ መስፈርቱ ወጥቶ ያልተካተቱ ሀገሮች መካተት አለባቸው የሚል አተያይ አለን። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያና እስራኤል የሌሉበት ዓይነት የትብብር ማዕቀፍ ሊሳካለት የሚችል አይሆንም።

አዲስ አበባ በተካሔደው ኮንፈረንስ ላይ እንደ ትልቅ ምሳሌና እንደ ምርጥ ተሞክሮ የተነሳው ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ወይም በአፍሪካ ቀንድ ሽብርተኝነትን በመከላከል ያደረገችው መስዋዕትነት ነው። ስለዚህ ዓላማው ይህ እስከሆነ ድረስ ኢትዮጵያን ማግለል ለምን አስፈለገ? እስራኤልንስ ማግለል ለምን አስፈለገ? የሚል ሐሳብም ተነስቷል። በተወሰነ መልኩ እንኳ ቢሆን ወገንተኝነት የሚንጸባረቅባቸው መስፈርቶች መቀመጥ የለባቸውም።

ለወደፊቱ እንደዛ ዓይነት መድረኮች ሲዘጋጁ ወገንተኝነት ከተጫናቸው ውጤታማ አይሆኑም። ስለዚህ ውጤታማ እንዲሆኑ አካታች የሆነ መስፈርት መካተት መቻል አለበት። እንደሚታወቀው ደግሞ የቲንክ ታንክ ሚና ለፖሊሲ አውጪዎች ነድፎ ማቅረብ ነው። እኛም የፈለግነው በዛ መልክ ቀርቦ እንዲሰማ ነው። ከዛ አኳያ ስንመለከተው ኮንፈረንሱ ውጤታማ ነበር።

ለወደፊቱ የቀይ ባህር ፎረምም ሆኑ ሌሎቹ ተከልሰው አካታች የሚሆንበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። የጋራ ደህንነት ደግሞ በተወሰኑ ሀገራት ብቻ የሚሸፈን አይደለም። ከጽንሰ ሐሳቡ (Theory) ከተነሳን የብሔራዊ ደህንነት ውስብስ ጽንሰ ሐሳብ (National Security Complex Theory) የሚባል አለ፤ ጽንሰ ሐሳቡ የሚለው አንድ ሀገር ወይ የተወሰኑ ሀገራት ብቻቸውን ደህንነታቸውን መሸፈን አይችሉም። ስለዚህ ትብብር ያስፈልጋል። ለመተባበር ደግሞ የግድ የባህር በር መኖሩ እንደ አንድ መለኪያ ሊሆን አይገባውም።

በርግጥ ኢትዮጵያ ደግሞ ለቀይ ባህር ያን ያህል ሩቅ ናት ወይ የሚል ነገርም በኮንፈረንሱ ሲነሳ ነበር። ምንም ሆነ ምን እኛ በዛ አካባቢ ያገባናል። ለቀይ ባህር ቅርብ መሆናችን ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ደህንነት የከፈልነው መስዋዕትነት ጭምር ስላለ የባህር በር ያስፈልገናል።

ያስፈልገናል ስንል ከማን ነው የምንወስደው? እያልን አይደለም። እንዴት ነው ማግኘት የምንችለው? በሚለው ላይ ነው እየተወያየን ያለነው። ለወደፊቱም በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ብቻም ሳይሆን በሀገራችንም እንዴት ነው ልንሔድበት የምንችለው በሚለው ላይ መመካከር ይኖርብናል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት የተጀመረው መድረክ ቀጣይነቱ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር አማረ፡-** ይህ መድረክ የመጀመሪያው የቀይ ባህር የትብብር መድረክ ነው። ቀጣዩ ኢትዮጵያ ውስጥ አሊያም የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች ውስጥ አሊያም እስራኤል ወይም ደግሞ ሳዑዲ ውስጥ ሊካሔድ ይችላል። ዋናው ነገር ግን ጀማሪዎቹ እኛ ነን። ተነሳሽነቱን ወስደናል፤ መድረኩ በዚህ ሁኔታ ቀጥሎ ፖሊሲ አውጪዎች ላይ ጫና ማድረግ አለብን። ወደጋራ ተጠቃሚነትና ወደጋራ ደህንነት መምጣት ይኖርብናል። ያንን ለማድረግ ደግሞ እንደእነዚህ አይነት ፎረሞች ያስፈልጋሉ የሚል ስምምነት ላይ ተደርሷል። ስለዚህ ምናልባት ከአራትና አምስት ወር በኋላ እንዳልኩሽ በአንዱ ሀገር ላይ ይዘጋጃል ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ማበርከት የሚያስችላት ብዙ ነገር እንዳለ ሁሉ ባለመግባቷ ደግሞ የምታጣው ምንድን ነው?**

**ዶክተር አማረ፡-** ባለመግባታችን የምናጣው ነገር ይታወቃል። ገና ለገና ስለ ቀይ ባህር ስላነሳን ብቻ የተፈጠረው ነገር የሚታወቅ ነው። ስለዚህ የፎረሙ አባል ሀገራት በሚነጋገሩበት ወቅት በምን ጉዳይ ላይ እንደሚነጋገሩ ኢትዮጵያ ማወቅ አትችልም። ሙሉ በሙሉ አባል እንኳ ባንሆንና ውሳኔ መስጠት ባንችልም ምን እየተካሄደ ስለመሆኑ አናውቅም።

በአሁን ወቅት ደግሞ ከኮንፈረንሱም አስቀድሞ በዚህ ዓመት ከባህር በር ጋር ተያይዞ ልናጠናው ያሰብነው ጉዳይ አለ። በመሰረቱ የወደብ አልባነት ሃሳብ በብዞዎቻችን ውስጥ ሰርጿል።

ሰው ወደብ የማግኘትን ጉዳይ ከመሬት ጋር ብቻ ያገናኘዋል። ነገር ግን በጣም ብዙ መንገዶች አሉ። እነዛን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር እንዴት መጠቀም አለብን በሚል ለማጥናት ያሰበነው ርዕሰ ጉዳይ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በቀይ ባህር ቀጣና የኃያላን ሀገራት ፉክክር ኢትዮጵያ ላይ የሚያሳርፈው ጫና እንዴት ይገለጻል? መፍትሔውስ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶክተር አማረ፡-** በርግጥ ለብዙዎች በቀጣናው አካባቢ ጥሩ ስላለ ብቻ ፍርቻ አለ። በርግጥ የሚያስፈራ መሠረት አለው። በአግባቡ ከገመገምነውና ትኩረት ከሰጠነው በአካባቢው መሰባሰባቸው የራሱ የሆኑ ተጽዕኖ አለው። ዝም ብሎ ደግሞ የሚፈራም አካል አለ። ነገር ግን በአግባቡ መተንተን አለበት። አንዱና ዋንኛው ግን አስቀድሜም ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ወታደራዊ የጦር ማዘዣዎች በአካባቢው መኖራቸው በቀጣናው ያሉ ሀገራት በራሳቸው እንዳይወስኑ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ አለው።

በተለይ ከነበራቸው የቅኝ ተገዥነት የተነሳ ፍራቻ ያለበት አካባቢ ነው። ምናልባት ይህ ጉዳይ እኛን ላይመለከት ይችል ይሆን እንደሆን አላውቅም። ዞሮ ዞሮ ግን እኛንም ስጋቱ ይደርሰናል። አንደኛውና ዋነኛው ሀገራቱ በነጻነት ገለልተኛ ሆነው በሀገራቸው የውስጥ ጉዳይና ቀጣናቸው ላይ እንዳይወስኑ እንደ አንድ መሰናክል ይሆን ይሆናል ወይ የሚያስብል ነገር አለ። በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባቱም ነገር ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ሀገራቱ ነጻ ሆነው ከመወሰን አንጻር ጫና ይኖረዋል።

ሌላው የውክልና ጦርነት ነው። በአንድ ወቅት አሜሪካና ራሺያ ኢትዮጵያንና ሱማሊያን እንዳዋጉት ሁሉ አሁንም ቢሆን ኃያላን የሚባሉ ሀገራት ብቻ ሳይሆኑ አስቀድሜ የጠቀስኳቸው አዳዲስ የመጡ የቀጣናው ኃያላን በአካባቢያቸው ያለውን ፉክክር አምጥተው ሊያራግፉብን ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በአካባቢው መሰባሰባቸው ዞሮ ዞሮ ለእኛ ስጋት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መፍትሔውስ ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**ዶክተር አማረ፡-** መፍትሔው ያው ቀጣናዊ ትብብር ነው። ኮንፈረንስ የማዘጋጀታችንም ምስጢር እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ ለመነጋገርም እንዲያመች ጭምር ነው። እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በእኩልነት እንዴት ማስተዳደር እንችላለን? የሚለውን ለማጠናከር ቀጣናዊ ትብብሮችን በአግባቡ ማጠናከር አስፈላጊ ነው። ከዛ በመነሳት ደግሞ የትብብር ማዕቀፎችን ዲዛይን ማድረግ ያስፈልጋል። ተጠቃሚነትም መኖር አለበት። ጉዳዩ ገና ሲነሳ ‹‹ውሃችንን ልትወስዱ ነው›› ከመባባል ባለፈ የጋራ ተጠቃሚነታችንን ጉዳይ እንዴት አድርገን ነው ማጠናከር ያለብን በሚለው ላይ መወያየት መልካም ነው። የጋራ ተጠቃሚነት ከሌለ ግጭቶች ይኖራሉ። ይህ ደግሞ እነርሱን ተጠቃሚ ያደርጋል። በውክልና ይገቡና መንግሥት የመመስረት ዓይነት ነገር ይኖራል። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ ሁሉ ለመቆጣጣር ቀጣናዊ ትብብር ወሳኝ ነው።

ምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ቀጣናዊ ትብብር እንደሌላው አካባቢ ብዙ ጠንካራ የሚባል አይደለም። ስለዚህም ማጠናከር ያስፈልጋል። ከማጠናከር አኳያ ሲታይ ደግሞ ከዚህ በፊት ጠንካራ ሚና ስትጫወት የነበረች ኢትዮጵያ ናት። እንዲህ ስል የሌሎቹን ሚና እውቅና ለመንፈግ ፈልጌ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- የባህር በር ጉዳይ ቢጠፋ ቢጠፋ ሰጥቶ በመቀበል መርህ ድረስ ሲሄድ እንደሚችል መገለጹ ይታወቃል። ይህ ምን ያህል አዋጭ ነው ይላሉ?**

**ዶክተር አማረ፡-** ይህ አባባል እንደሚመስለኝ ምናልባት የተገለጸበትን መንገድ ሰው በአግባቡ ካልተረዳው በስተቀር ጥሩ ነው። እኛ የተቸከልነው መሬት በሚለው ላይ ነው። እኛ ብቻ አይደለንም፤ ሌሎቹም ማለትም የባህር በር ሊያጋሩን የሚችሉ ሀገራት የተቸከሉት መሬት የሚለው ነገር ላይ ነው። እኛ ልንሰራቸው ካቀድናቸው የምርምር ሥራዎች ውስጥ አንዱ የባህር በር እንዴት ነው የምናገኝበት አማራጭ ማስፋት የምንችለው? የሚል ነው። ዘዴዎቹና ተሞክሮቹስ ምንድን ናቸው? የሚለውን ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃሳቡን ያነሱበት መንገድ ግን ጥሩ ነው ብዬ አስባለሁ።

ከብዙ መንገዶች አንዱ በኮሪዶር መጠቀም የሚለውን ማንሳት ይቻላል። ለኮሪዶር ደግሞ መሬት ለመስጠት ምንም ችግር የለውም። እሱ ማለት ደግሞ ዓለም አቀፍ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን እንደመዘርጋት ማለት ነው፡፡ ኮሪዶር የሚሰራባቸው ሀገሮች አሉ። ለምሳሌ አዛርባጃን የባህር በር የላትም። ነገር ግን በሌላ ሀገር ላይ ኮሪዶር በመገንባት የባህር በር ተጠቃሚ የምትሆንበትን እድል ፈጥራለች። ከዚህ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስተሩ እንዳሉት ሌላ ነገር ሰጥቶ መቀበል ይቻላል። ይህ ግን በተለያዩ ጥናቶች የሚመለስ ነው ብዬ አስባለሁ። በጣም ብዙ አማራጮች ስላሉ መንገዱ ዝግ አይደለም። እንዲያው አንዱ ላይ ብቻ ከምናተኩር የተለያየ ዓይነት አማራጭ ቢኖረን እኛንም ሀገራቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። በጣም የሚያስገርመው ነገር ሌሎች ሀገር ወደአካባቢው ሲመጡ መሬቱም ቢሆን ሲሰጣቸው ይታያል። ለምሳሌ አሜሪካ በብዙ ሺ ማይልስ ርቀት መጥታ ጂቡቲ ላይ መሬት አላት። ጃፓንና ቻይናም እንዲሁ በብዙ ሺ የሚቆጠር ማይልስ አቋርጠው መጥተው ወይ ጂቡቲ ላይ ወይም ደግሞ ኤርትራ ላይ መሬት አላቸው።

ታዲያ የአፍሪካ ሲሆን ልዩነቱ ምንድን ነው? ቢሆን የተባለው እንኳ በሊዝ፣ በኮሪዶርና መሰል ነገሮች ነው። ይህን ማድረግ የሚቻለው ግን ቀጣናዊ የሆነ ትብብር ሲኖር ነው። ለምሳሌ መሬቱ ለኢትዮጵያ በተለያየ መንገድ ቢሰጥ የሚለው ሃሳብ አልተገዛም። ለአሜሪካኖቹ አሊያም ለሌሎቹ ሀገራት እንደሚሰጠው ሁሉ ለኢትዮጵያ እንስጥ የሚለው ሃሳብ በሌላውም ዘንድ አልተገዛም። እኛም እስካሁን አልገዛነውም። ይህ በጥናት መደገፍ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆኗ ባለችበት ቀጣና ተጽዕኖ መፍጠር እንዳትችል አድርጓታል የሚሉ አሉ። እርስዎ ይህን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር አማረ፡-** በቀጣናው ለረጅም ዘመን ተጽዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉ ሀገራት ቀዳሚዋ ኢትዮጵያ ነበረች፤ ነችም። በእርግጥ እንዳልሽው በአሁኑ ወቅቱ በቀጣናው ድሮ እንጫወት የነበረን ሚና እየተጫወትን አይደለንም የሚሉ አካላት አሉ። ለምሳሌ ድሮ ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበርነው ምን ምን በማድረግ ነው? ብለው መቁጠር የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በርግጥ በተወሰነ መልኩም ቢሆን መቀዛቀዞች ይኖራሉ። ምክንያቱም ትኩረታችን ወደ ውስጥ ችግሮቻችን ላይ ነው፡፡ እሱንም ለመቅረፍ እየተሰራ ነው። እንዲያም ሆኖ ወደቀደመው ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን የማንመለስበት ምክንያት የለም።

ከወደቡ ጋር ተያይዞ ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን ብዙ ግንኙነት አለው ለማለት ይከብደኛል። እርግጥ ነው ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አንጻር እና እድገቱን ከማቀላጠፍ አኳያ እንዲሁም መሰል ጉዳዮች ላይ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ። ቢሆንም ከተጽዕኖ ፈጣሪነታችን የዚያን ያህል ቀንሶናል ብዬ ለመናገር አልችልም። እንዲያም ሆኖ የባህር በር አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።

ወደብ አልባ መሆን ከባድ ነው። ብሔራዊ ምስጢርን መጠበቅ አይቻልም። የምናስገባቸው ነገሮች ላይ ቁጥጥር ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ ከምንችለው በላይ ቀረጥ በተፈለገው ጊዜ ሊጨመርብን ይችላል። በተጨማሪም የምንፈለገውን ነገር በፈለግነው ጊዜ ላይገባልን ይችላል። መዘግየቶች ይኖራሉ። መዘግየት ሲኖር ደግሞ የስቶር ኪራይ መክፈል ይመጣል። እነዚህ ነገሮች ተፈትተው ወደ ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን ማማ ላይ የበለጠ እንቀመጣለን ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር አማረ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የቱሪዝም ሀብቶችን ለማስተዋወቅ የተዘጋጀችው የቁንጅና ውድድር አሸናፊ


**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወጣት ማኅደር ፍቃዱ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው የአትሌቶች መፍለቂያ ተብላ ከምትጠራው አርሲ በቆጂ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በአርክቴክቸር አግኝታለች። ከልጅነቷ ጀምሮ ከምታየው ነገር በመነሳት በቁንጅና ውድድር ላይ የመሳተፍ ፍላጎት ነበራት። ‹‹ቪዝት ኦሮሚያ›› የተሰኘው የቁንጅና ውድድር ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ግን የመወዳደር ፍላጎቷ እየጨመረ በዘንድሮ ውድድር እንድትሳተፍ መነሳሳትን ፈጥሮላታል። ለውድድሩ የሰጠችው ትልቅ ትኩረት፣ ውስጣዊ ፍላጎትና በራስ መተማመን ለአሸናፊነት እንዳበቃት የምትናገረው ማኅደር ፍቃዱ የዘንድሮው ሚስ ቱሪዝም ኦሮሚያ አሸናፊ ናት።

ማኅደር፤ ከዚህ ቀደም በተካሄዱ የሞዴሊንግ ወይም የቁንጅና ውድድሮች ላይ ተሳትፋ ባታውቅም የመሳተፍ ውስጣዊ ፍላጎቱ ግን ነበራት። እስከ አሁን ሙሉ ጊዜያዋንና አቅሟን ለትምህርቷ አድርጋለች። ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ግን ውድድሩን የመቀላቀል ፍላጎቷ ጨምሮ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ባጠናቀቀች ማግስት ፊቷን ወደ ቁንጅና ውድድር አዞራለች።

‹‹በኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የሚዘጋጀው ውድድር ከተጀመረ አንስቶ የመወዳደር ህልምና ጉጉት ነበረኝ›› የምትለው ማኅደር፤ ኢትዮጵያ እጅግ አስገራሚና የታወቁ የቱሪዝም መስዕቦች ያሏት ውብ ሀገር መሆኗን ጠቅሳ፣ ሀብቷን በአግባቡ መጠቀም እንዳልተቻለ ነው የገለጸችው። ለዚህም ሀገሪቷ ያላትን ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት በማስተዋወቅና መጠቀም ላይ ብዙ የሚቀሩን የቤት ሥራዎች አሉ ትላለች። እዚህ ላይ ብዙ መሥራት እንደሚገባም ነው ያስገነዘበችው፤ ‹‹እኔም ሙያዬን ተጠቅሜ ባለኝ አቅም የቱሪዝም መስህቦችን የማስተዋወቅ ፍላጎቱ ቀድሞውኑ በውስጤ ስለነበር ውድድሩን ለመሳተፍ እድሉን ሳገኝ ለመጠቀም ችያለሁ›› ትላለች።

‹‹በቁንጅና ውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ስመዘገብ ጀምሮ አእምሮዬ ለሁሉም ነገር ዝግጁ ነበር። በራስ መተማመንን መጨመርና ስለውድድሩ በደንብ ማወቅ በራሱ ውድድሩን



50 በመቶ የማሸነፍ ያህል በመሆኑ ይህን ለራሴ በደንብ ነገሬው ራሴን አሳምኜ ስለነበር ለማሸነፍ ዝግጁ ነበርኩ›› የምትለው ማኅደር፤ በውድድሩም የጠበቀችው እንደገጠማትና ያሰበችው ተሳክቶላት ማሸነፏን ተናግራለች።

ማኅደር እንደምትለው፤ ኮሚሽኑ ለውድድሩ የተለያዩ መስፈርቶች አዘጋጅቷል። የመጀመሪያው የቁመት፣ የክብደት እና ሦስት ቋንቋዎችን (አፍን ኦሮሞ፣ አማርኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች) መናገር መቻል እና መሰል መስፈርት ነበር። ከዚህ በኋላ ስለቱሪዝም በሦስቱ ቋንቋዎች የመገለጽ ፈተናም የውድድሩ አካል እንደነበር ታስታውሳለች። እንዲህ እንዲህ እያለ በመጨረሻ በመድረክ ላይ በሚደረገው ውድድር ላይ በኦሮሚያ ካሉት 21 ዞኖች የደረሳትን የአንዱን አካባቢ የቱሪዝም መዳረሻዎች ባህላዊ አለባበስና መሰል ሀብቶች በመግለጽ አስተዋውቃለች። ልዩ ተሰጥኦን ማሳየትም ሌላኛው የውድድሩ አካል መሆኑን ጠቅሳ፤ የመጨረሻው ፈተና በመድረኩ ላይ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በመመለስ ስለነበር በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ አልፋ ማሸነፍ ችላለች።

ወደ ውድድሩ ከመግባቱ አስቀድሞ በክልሉ ስላሉ የቱሪዝም መስህቦች በደንብ ማወቅና መዘጋጀት ተጠባቂ ተግባር ነው የምትለው ማኅደር፤ ‹‹እኔ የደረሰኝ የጉጂ አካባቢ ባህላዊ አልባሳትን እና የቱሪዝም መስህቦችንና መዳረሻዎችን በሚገባ ተረድቶ ማስረዳትና ማስተዋወቅ ነበር ትላለች። ባህላዊ አልባሳቱን ለብሳ በማሳየት፤ ስለመዳረሻዎቹና ስለባህላዊ አልባሳቱ በሚገባ በመግለጽ ማስተዋወቅ ችላለች።

እሷ እንዳለችው፤ የሚስ ቱሪዝም ኦሮሚያን ውድድር ማሸነፌና የኦሮሚያ የቱሪዝም አምባሳደር በመሆኔ ብዙ ሥራዎች ይጠብቃታል። ከክልሉ ቱሪዝም ኮሚሽን ጋር በመሆኑን እንደ ብራንድ አምባሳደር የቱሪዝም ሀብቶች፣ መስህቦችና መዳረሻዎችን ማስተዋወቅ፣ ስለቱሪዝም ህብረተሰቡ በቂ መረጃ እንዲያገኝ፣ ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን መጥተው እንዲጎበኙ ማድረግ ይኖርባታል። የተለያዩ ሃሳቦች ላይ የተለያዩ አዲዲስ ነገሮች በመፍጠር በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ የክልሉ የቱሪዝም መዳረሻዎች ተቀዳሚ የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲሆኑ መሥራትም ይኖርበታል።

እንዲህ ዓይነት የቁንጅና ውድድሮች መዘጋጀታቸው በተለይ ወጣቶች በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር ያደርጋል የምትለው ማኅደር፤ በተለይም ባሉት የቱሪዝም ሀብቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንደሚገባ ጠቁማለች። በሌሎች ዘርፎችም እንዲሁ ያሉ ብዙ ሥራዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያግዝ መሆኑን ገልጻለች። የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ ያለን እውቀት ለማዳበርና የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎችን ለመውሰድ ራሳቸውን ማሻሻልና ማሳደግ ላይ እንዲሰሩ የሚያበረታታ እንደሆነና የሚፈልጉትን አድርገው ማሳየት እንዲችሉ እድሉን እንደሚፈጥርም አመልክታለች።

‹‹ሰዎች ስለቁንጅና ወይም ስለውበት ያላቸው አመለካከትና አገላለጽ ይለያያል። ቁንጅና የአፍንጫ፣ የጸጉር እና የሌሎች መገለጫ ብቻ አይደለም፤ ሁላችንም የምንስማማበት አንድ ዓይነት መገለጫ የለውም›› የምትለው ማኅደር፤ ‹‹እንደኔ አመለካከት ቁንጅና ወይም ውበት በሚጠበቅብኝ ቦታ ላይ የሚጠበቀውን እውቀት ይዞ መገኘት ነው። ›› ብላለች። በየጊዜው እውቀትን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ አዳዲስ ነገሮችን መሞከር እና የራስን አቅም ማጎልበት ከዘመኑ ጋር አብሮ መጓዝ መቻል እና እነዚህ ነገሮች ማሳካት መቻል እኔ ቁንጅና ወይም ውበት ነው ብዬ አምናለሁ›› ብላለች።

በወጣቶች ዘንድ ብዙ ጊዜ ያልተለመደው በራስ መተማመን መቻል ነው የምትለው ማኅደር፤ ‹‹ስለራሳችን በሙሉ ራስ መተማመን መንፈስ ስላለን ስለምናውቀው ነገር በመናገር ራሳችንን መግለጽ ካልቻልን ማንም ሰው ስለኛ ጠንካሬና ጉብዝና ሊናገርልን አይችልም›› ነው የምትለው።

ማኅደር እንደምትለው፤ አሁን ላይ ዘመኑ ነገሮች በቀላሉ ፈልጎ ለማግኘት፣ ለመማር የተመቸ ስለሆነ እነዚህን አማራጮች በመጠቀም በትምህርትም ሆነ በሥራ ራስን ብቁ አድርጎ ከዓለም ጋር እኩል መራመድ መቻል ከወጣቱ የሚጠበቅ ትልቁ ጉዳይ ነው። ‹‹እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ፍላጎቱ ካለን፣ ማድረግ የምንፈልገውን በእቅድ የምናደርግና በቁርጠኝነት የምንፈጸም ከሆነ ካሰብነው እንዳንደርስ የሚያደርገን ነገር የለም›› ትላለች።

ማኅደር እንዳለችው፤ አሸናፊ ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ የክልሉ የቱሪዝም አምባሳደር ሆና ታገለግላለች። በዚህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዘርፉ የራሷ ትልቅ ዐሻራ ማሳረፍ ትፈልጋለች። በቱሪዝም ዘርፉ ስኬቶች እንዲመዘገቡ መሻሻሎች እንዲመጡ፣ አዳዲስ ነገሮች እንዲፈጠሩ እና ካሉት የቱሪዝም ሀብቶች መጠቀም እንዲቻል የሚያደርጉ ሥራዎችን ጠንክራ ትሰራለች።

የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በርካታ ኢንቨስትመንቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲመጡ የሚያደርግ ዘርፍ ነው። ማኅደርም የተመረቀችበትን የአርትቴክቸር ሙያም ተጠቅማ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው አንድ ርምጃ ወደፊት እንዲጓዝ ለማድረግ አቅዳለች።

‹‹ለውጥ ከራሳችን የሚጀምር በመሆኑ ያሉንን ሀብቶች ማሳየት፣ እርስ በእርስ በመማማር እና በአካባቢያችን ያሉትን ሰዎች ማስተማር ስንችል ከፍ እያልን ዓለም አቀፍ ደረጃ መድረስ እንችላለን›› የምትለው ማኅደር፤ ሁላችንም ከአካባቢያችን ጀምረን ያለንን ማወቅና ማሳወቅ ላይ ትኩረት ሰጥተን መሥራት አለብን ስትል ታስገነዝባለች። ይህን በማድረግም ራሳችንንም ሀገራችንንም መጠቀም መቻል አለብን የሚል ጽኑ እምነት እንዳላትም ተናግራለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ልብ ወይንስ ዓይን ?

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ማለዳውን የአስፓልት መንገዱን ይዘው የሚከንፉ መኪኖች ረፋዱ ላይ ቁጥራቸው ይጨምራል። ለነገሩ የመኪኖቹ ጉዞ ጠዋት ላይ ብቻ አይደለም። ሌሊቱን ሙሉ ሲጓዙ ማደር ልማዳቸው ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ታዲያ ስለፍጥነታቸው ገደብ ደንታ ላይኖራቸው ይችላል። የሌሊቱ ጭርታ ከግርግር የጸዳ ስለሚመስላቸው ባሻቸው አካሄድ ይጓዛሉ።

መቼም በዚህ ሰዓት መንገድ የሚጀመሩ ሾፌሮች ልክ እንደ ቀኑ ውሎ መንገደኛ ይኖራል ብለው አያስቡም። ያስባሉ ቢባል እንኳን ዜብራ ላይ ቆመው ቅድሚያውን ለእግረኛ እንስጥ ላይሉ ይችላሉ። የሆነ ሆነና ቀንም ይሁን ሌሊት ጥንቃቄን መላበሱ አይከፋም። ተረቱም እኮ ‹‹አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዝ›› ይላል።

‹የመንገድን ነገር መንገድ ያነሳዋል› እንዲሉ ከሰሞኑ በመንገዴ ላይ የታዘብኩትን አንድ እውነት ‹‹እነሆ!›› ለማለት ወደድኩ። ቦታው ከጀሞ አንድ ወደ ሜክሲኮ በሚወስደው አቅጣጫ ላይ ይገኛል። ይህ መንገድ በቅርቡ ተጨማሪ ሆኖ የተገነባ ሶስተኛ መንገድ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በወጉ ተጠናቆ ሥራ አልጀመረም እንጂ እንደታሰበው ከዓላማው ቢገናኝ በርከት ያሉ ችግሮችን ያቃልል ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል ጀምሮ መተው ለመደብንና የዚህንም ታላቅ መንገድ ጠቀሜታ ሳናጣጥመው ቀረን።

ወዳጆቼ! አሁንም በዚሁ መንገድ ላይ ነኝ። ሳምንቱን ሙሉ ጠዋት ማታ ሳልረግጠው አላልፍም። ጉዞዬ በመኪና ቢሆንም ዓይኖቼን ጣል አድርጌ ማማተር ለምዶብኛል። ታዲያ ይህ ልምዴ ከብዙ አጋጣሚዎች ሲያገናኘኝ ቆይቷል። በአንዳንዱ አስቃለሁ፣ አዝናለሁ እገረማለሁ።

ከሰሞኑ ያጋጠመኝ ግን ለእኔ ከሁሉም ይለያል። በዚሁ አዲስ መንገድ ላይ ያየሁት እውነት ብዙ ሲያሳዝነኝ፣ ሲያስገርመኝ ቀናት ተቆጥረዋል። አሁንም በየቀኑ እያየሁት ነውና ከነግርምታዬ ቀጥያለሁ። ወደ ዋናው ጉዳይ ልውሰዳችሁ ። በዚሁ የጀሞ መንገድ የግራ አቅጣጫ የአዲሱ መንገድ አካፋይ ላይ።

መንገዱ አሁንም እንዳማረበት ተዘርግቷል። ይህ ጅምር መንገድ ባሳለፍነው የክረምት ጊዜ ብዙ ጫናዎች አሳልፏል። ከባድ መኪኖች፣ ትንሽ ትልቅ ተሽከርካሪዎች፣ ፈረስ ጋሪዎች ባጃጆች፣ እግረኞች እንዳሻቸው ረግጠውታል። አፍ የለውም እንጂ አፍ ቢኖረው ኖሮ ግማሽ አካሉ ፈርሶ ሲቦረቦር የጎርፍ ውሃ ሲሞላውና ሲሰነጣጠቅ ‹‹በሕግ አምላክ›› ባለን ነበር። ግን ማለት አልቻለም። ዛሬም ከነሽክሙ ሊቀጥል ተገዷል።

የክረምት ወራት አልፎ መስከረም በባተ ማግስት ደግሞ የዚህ መንገድ ዓላማ በሌላ ገጽታ ተገልጧል። የመንገዱ ያልተደፈነ አካፋይ እንደ ምቹ አልጋ እንደ ሰፊ እልፍኝ ሰዎችን አስተኝቶ ማሳደሩን እያሳየን ነው። ‹‹ማሳደር›› ሲባል ደግሞ ለጊዚያዊ ዕንቅልፍ ብቻ እንዳይመስላችሁ። ስፍራውን የመረጡ ጥቂት የጎዳና ተዳዳሪዎች ከበላዩ ጣራ ቢጤ ሰርተው ፣ ዙሪያውን በካርቶን መሰል ግርዶሽ ከልለው ውለው ያነጉበታል።

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ በዚህ የመንገድ አካፋይ እስከዛሬ ጥቂት የማይባሉ መኪኖች አቅጣጫ በመሳት፣ አደጋ ሲያደርሱ ተስተውሏል። ይህ በሆነበት አጋጣሚ ሁሉ ጎማቸውን ይዞ ሚዛናቸውን የሚያስተው ደግሞ ይኸው የመንገድ ላይ አካፋይ ነው።

አሁን ደግሞ ዓይናችን በዚሁ ጥግ ጎጆን የቀለሱ ነፍሶች የሞት ቀናቸውን ሲጠባበቁ እያሳየን ነው። ይህ ምሽግ መሰል አካፋይ ከእይታ የተከለለ፣ ሚስጥር የለውም። ማንም ጠጋ ብሎ እውነቱን ላረጋግጥ ቢል ገሀዱ ወለል ብሎ ይታየዋል። ጉዳዩን ያዩ ግን ሁሌም እንደዋዘ ዝም እያሉ ነው። እንደእኔ ይህ ዓይነቱ መዘናጋት ዋጋ ማስከፈሉ አይቀርም።

ርግጥ ነው እነዚህ የጎዳና ላይ ነፍሶች ጎናቸውን ማሳረፊያ ጥግ ያጣሉ። በየስፍራው ኩርምት ብለው ሌሊቱን ማንጋታቸውም ብርቅ ሆኖ አያውቅም። ጎዳና የወጡ ልጆች ጎናቸውን ሲያሳርፉ እንደሌሎቻችን የሚቀድማቸው ጣፋጭ ዕንቅልፍ አይደለም። ካሉበት ቦታ ጋር ተያይዞ ብዙ መከራዎችን ይገፋሉ። ለብርዱ ሲሉ የሚወስዷቸው አንዳንድ ነገሮች የዕድሜ ልክ የጤና እክሎቻቸው ናቸው። መደፈር፣ ለሌሎች ወንጀሎችና አሳሳቢ ለሚባሉ ስጋቶች መጋለጥ ከሕይወታቸው የማይነጠሉ ሀቆች ሆነዋል።

አሁን ላይ ደግሞ ችግሩ ይህ ብቻ አልሆነም። የእነሱ ማረፊያ ለአደጋ መጋለጡ ከተለመደው የኑሮ ልምዳቸው ለየት እያደረገው ነው። ጎማ ስር ተነጥፎ፣ አስፓልት ላይ ተዘርግቶ ራስን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ የሚቻል አይደለም። አይበለውና ሌሊት ላይ በሚከንፉ መኪኖች አደጋ ቢያጋጥም እንኳን ስለእነሱ ሕይወት ማንም ግድ የሚለው ያለ አይመስልም።

በጣም የሚገርመው ጉዳይ በእነዚሁ ልጆች የማረፊያ አካባቢ የሚያዘወትሩ የትራፊክ ፖሊሶች ነገር ነው። ትራፊኮቹ ሁሌም ቢሆን ከአጠገባቸው ቆመው አላፊ አግዳሚ መኪኖችን ያስተናግዳሉ። ሕግ የጣሰ፣ ደንብ የተላለፈ አሽከርካሪ ቢኖር ይቀጣሉ፣ ይገስጻሉ። ልብ በሉ ይህ ሁሉ የሚሆነው የጎዳና ልጆቹ ተደራርበው በሚተኙበት የመንገድ አካፋይ ላይ ነው።

ይህ ሁሉ ሲደረግ ትራፊኮቹ ለአፍታ መለስ ብለው የልጆቹን ስጋት አይጋሩም። ሁኔታቸውን በየቀኑ ቢያስተውሉትም ግዴለሽነት ይሁን ወይም ሌላ ስለነሱ ደንታ ሰጥቷቸው አያውቅም። ምን አልባት ይህን ጉዳይ ደፈር ብዬ መናገሬ ያለ ምክንያት አይደለም። እነሱ ስለነዚህ ወገኖች ግድ የሚላቸው ቢሆን ኖሮ ሞት እንደተጋረጠባቸው እያዩ ዝም አይሉም ነበር። በላያቸው ላይ ከከባድ እስከ ቀላል መኪኖች ሲያንዣብቡባቸው እያስተዋሉም ባላየ አያልፉም ነበር።

አንዳንዴ ስለሰዎች ደህንነት ሲባል ተገቢውን ኃይል መጠቀም የሚያስወቅስ አይሆንም። እናት አባትም ቢሆኑ እኮ ልጆች ሲያጠፉ ቢቆነጥጡ ቢገርፉ ለክፋት አይደለም። ስለነገው መልካምነት እንጂ። የትራፊኮቹም ጉዳይ እንዲሁ ቢሆን ተገቢ ነበር።

እነሱ በዋናነት ከቆሙለት የትራፊክ ሙያ ባሻገር ፖሊስ መሆናቸው ብቻ በብዙ ተግባራት ያስልፉቸዋል። ሙያቸው የታጠረው መኪኖችን በመዳኘት ብቻ ሳይሆን እንደ ማንኛውም ፖሊስ ሕግን በተገቢው መንገድ በማስከበር ጭምር ነው። ይህ እውነታ ደግሞ ስለጎዳና ሕጻናት ደህንነት ጭምር ያገባቸዋል ማለት ነው።

በእኔ ግምት የትራፊክ ፖሊሶቹ ችላ ባይነት ሌሎች ሰዎች ስለልጆቹ ያገባኛል እንዳይል ሰበብ የሆነ ይመስላል። ፖሊስን የመሰለ ሕግ አስከባሪ ባለበት ሀገር መስመር አልፎ ስጋት ላይ ያሉትን ልጆች ለማንሳት ማስገደድ የሚቻል አይመስለኝም። ጉዳዩ በሚመለከታቸው የሕግ አስከባሪዎች ፊት ግን ቀላል ይሆናል።

‹‹ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› ይሉት አባባል ለጤናው ጉዳይ ብቻ የተቸረ ምሳሌ አይደለም። እንደውም በትራፊክ አደጋ ለሚደርሰው የሕይወት መጥፋት የቀረበ ጥቆማ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህ ዓይነቱ ሀቅ ግን በጎዳና ወድቀው አደጋን ሊቀበሉ ለተዘጋጁት ነፍሶች ይሰራ አይመስልም።

አያድረሰውና አንድ ቀን እነዚህ ምስኪን ልጆች ለዚህ ስጋት ተጋልጠው ቢገኙ ‹‹ወይኔ፣ ተነስተው ቢሆን ኖሮ ›› ከሚል የተለመደ ጸጸት እንደማናልፍ ዕሙን ነው። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ዓይን ብቻ ሳይሆን ልብ ጭምር አስተውሎ መፍትሔ ሊሰጣቸው ይገባል።

በየቀኑ ተደራሽ የሚደረገው የትራፊክ አደጋ ሪፖርት የራሱ ምክንያትና መነሻ አለው። ሁሌም በሾፌሮች ቸልተኝነት፣ በእግረኞች ስህተት፣ በመኪኖች ቴክኒክ ችግር የሚለው ቃል ሰልችቶናል። አባባሉ ከትራፊክ አደጋዎች በኋላ የሚሰማ ቃል ነው።

ይህ በጎዳና ላይ የሚስተዋለው ‹‹ጠብ ያለሽ በዳቦ›› የሞት ጥያቄ ግን ማንም ትኩረት ችሮት በየትኛውም መገለጫ ሲካተት ተሰምቶ አይታወቅም። ራስን ከአስፓልት አንጥፎ ሕይወት የሚነጥቅን አደጋ ‹‹ካልመጣህልኝ›› መባሉ ከማስገረም ባለፈ ከልብ ያሳዝናል። ትራፊኮቹም ቢሆኑ አደጋ ከመድረሱ በፊት መጠንቀቅ ያሻል የሚሉንን ጉዳይ በተግባር ሊያሳዩን ይገባል።

በየቀኑ የሞት ስጋት የተጋረጠባቸው ወገኖቻችን ከእነሱ ዓይኖች የራቁ አይደሉም። ዕለት በዕለት ያዩዋቸዋል። ተኝተው መነሳታቸው፣ ተነስተው መራመዳቸው፣ የአስፓልቱን አካፋይ ቤቴ ብለው የሙጥኝ ማለታቸውን አሳምረው ያውቁታል። ነገር ግን ማየት ማስተዋላቸው ብቻውን ፋይዳ የለሽ ነው። ልባቸው ሊወስን ሙያቸውም ሊፈርድ ይገባል። ዓይናቸው ልብ ሆኖ ነፍስ ሊያድን፣ ሕይወት ሊታደግ ግድ ይላል።

# ዓለም አቀፍ



## በሞዛምቢክ ወረርሽኝ ለመከላከል ከ45 ሺህ በላይ ዶሮዎች ተቃጠሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የወፍ ጉንፋን (በርድ ፍሉ) በሽታ ስርጭትን ለመከላከል ሲባል በደቡባዊ ሞዛምቢክ ከ45 ሺህ በላይ ዶሮዎች ታርደው ተቃጥለው እንዲቀበሩ ተደረገ።

ከደቡብ አፍሪካ የተነሳው የወፍ ጉንፋን የሚያደርሰውን ጉዳት ለመከላከል ነው ተብሏል። ዶሮዎቹም ወደ ሞዛምቢክ የገቡት ከአጎራባች ደቡብ አፍሪካ ነው።

ወረርሽኙ ሞራሙቤኔ በተባለ የሞዛምቢክ ግዛት መስፋፋቱ ተገልጿል።

ወደሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች ሊዛመት ይችላል የሚል ስጋት ስላለ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

የወፍ ጉንፋን ወይም በርድ ፍሉ በተለይም የዱር አእዋፍ የሚያጠቃ ሕመም ነው።

በንክኪ፣ በተበከለ ምግብና ውሃም ዶሮዎች በማቆያ ሳሉ በቀላሉ ሊሰራጭ ይችላል።

ይህ ወረርሽኝ መነሳቱ የእንቁላልና ዶሮ እጥረት አስከትሏል። ዋጋውም በሞዛምቢክ ንሯል።

ከ350 የሞዛምቢክ ሜቲካል ወደ 600 ነው በአንድ ጊዜ የዶሮ ዋጋ የጨመረው። እንቁላል ደግሞ ከ100 ሜቲካል 150 ገብቷል።

45ሺው ዶሮዎች እንዲወገዱ የተወሰነው በበሽታው ከተያዙ ዶሮዎች ጋር ንክኪ ስለነበራቸው እንደሆነ የሞዛምቢክ የእንስሳት ጥበቃ አስታውቋል።

ደቡብ አፍሪካ ገጥመዋት ከሚያውቁ ወረርሽኞች የከፋ የሆነውን ይህንን ወረርሽኝ ለመቆጣጠር እየሞከረች ነው።

በአጠቃላይ ሰባት ሚሊዮን እንቁላል የሚጥሉ ዶሮዎች እንዲገደሉ ዶሮ አርቢዎችን አስገድዳለች። ይህም ከአገሪቱ ዶሮዎች መካከል ከ20-30% ነው።

የሞዛምቢክ ብሔራዊ እንስሳት ጥበቃ ባለሙያው አሜሪኮ ዳ ኮንሴችዮ እንዳሉት ዶሮና የዶሮ ተዋፅዖ ከደቡብ አፍሪካ እንዳይገባ አግደዋል።

ወረርሽኙ በተነሳበት የሞዛምቢክ ግዛት ዶሮና እንቁላል ስርጭትም መቆሙን ቢቢሲ ዘግቧል።

## በጋዛ የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ የተመድ ኤጀንሲዎች ጥሪ አቀረቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) ኤጀንሲዎች በጋዛ ሰርጥ ውስጥ ያለው ሁኔታ እየከፋ መምጣቱን ተከትሎ ሰብዓዊ የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ ጥሪ አቀረቡ።

የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና የዓለም የጤና ድርጅትን ጨምሮ አምስት የተመድ ኤጀንሲዎች የጋዛን ሁኔታ “አሰቃቂ” ሲሉም በጋራ ባወጡት መግለጫ አስፍረዋል።

እስራኤል በሙሉ ከበባ ውስጥ አስገብቻታለሁ ባለቻት ጋዛ ሰርጥ የተጠናከረ ጥቃት እንደሚቀጥል እያስጠነቀቀች ባለችበት ወቅትም ነው የተባበሩት መንግሥታት ግጭቱ እንዲረግብ እየተማጸነ ያለው።

ግጭቱ ከተጀመረ ከሁለት ሳምንት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ 20 እርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በግብጽ የድንበር ማቋረጫ ራፋህ በኩል ወደ ጋዛ ገብተዋል።

ሆኖም በጋዛ ከሚያስፈልገው እርዳታ አንጻር “የውቅያኖስ ጠብታ” ሲሉም ተሟጋቾች ርዳታው አናሳ ነው ሲሉ ወቅሰዋል።

ከግጭቱ በፊት 500 የሚጠጉ ርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በየቀኑ ወደ ጋዛ ይገቡ እንደነበር የአክሽን ኤይድ የፍልስጥኤም ቃል አቀባይ አስረድተዋል።

በጋዛ ሰርጥ ከሚኖሩት መካከል ወደ 1.2 ሚሊዮን ነዋሪዎች በርዳታዎች ላይ ጥገኛ እንደነበሩም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መረጃ ያሳያል።

ከሁለት ሳምንታት በፊት ሐማስ በወሰደው ያልተጠበቀ ወታደራዊ እርምጃ 1ሺህ 400 ሰዎች በእስራኤል ተገድለዋል።

የሐማስ ታጣቂዎች በጋዛ ሰርጥ በኩል ድንበር ተሻግረው ነበር በንጹሐን እና በወታደሮች ላይ ጥቃት የፈጸሙት።

እስራኤል ላለፉት ሁለት ሳምንታት ቀን ተሌት ጋዛን በቦምብ በመደብደብ ላይ የምትገኝ ሲሆን በዚህም ከ4 ሺህ 300 ሰዎች በላይ ተገድለዋል። እስራኤል በቅርቡ እግረኛ ጦሯን እንደምታስገባም እየተጠበቀ ይገኛል።

እስራኤል ጋዛ ሰርጥን ሙሉ በሙሉ በመዝጋት ከበባ እንዲደረግ ያዘዘች ሲሆን፣ በጋዛ ‘ኤሌክትሪክ፣ ምግብ፣ ነዳጅ አይኖርም ሲሉም የእስራኤል መከላከያ ሚኒስትር ዮአቭ ጋላንት ባለፈው ሳምንት ትዕዛዝ መስጠታቸው ይታወሳል።

ጋዛ ሰርጥ ወደ 2ነጥብ3 ሚሊዮን የሚጠጉ ፍልስጥኤማውያን መኖሪያ ስትሆን፣ ለ16 ዓመታት ያህል የቆየ ከበባ ውስጥ ትገኛለች።

ቅዳሜ እለት ወደ ጋዛ የገባው የርዳታ አቅርቦት መድኃኒት፣ ምግብ፣ ውሃ እና የሬሳ ሳጥን ያካተተ ቢሆንም ነዳጅ አልነበረም።

የተመድ ኤጀንሲዎች ሕጻናት፣ ነፍሰ ጡሮች እና አዛውንቶች ለከፋ ችግሮች እንደተጋለጡ ጠቅሰው ከጋዛ ሰርጥ ሕዝብ ግማሽ የሚጠጉት ሕጻናት መሆናቸውንም አጽንዖት ሰጥተዋል።

ከተኩስ አቁም ስምምነቱ በተጨማሪም “በመላው ጋዛ አፋጣኝ እና ያልተገደበ የሰብዓዊ እርዳታ ተደራሽነት” እንዲሁም የረድዔት ድርጅት ሠራተኞች ለተቸገሩ ፍልስጥኤማውያን እንዲረዱ መፈቀድ አለበት ብለዋል።

“በጋዛ ሰርጥ ከ1.6 ሚሊዮን በላይ ፍልስጥኤማውያን አስቸኳይ ሰብዓዊ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል” ብለዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት

## የታላቁ አትሌት ቀጣይ ጉዞ

ብርሃን ፈይሳ

በፈረንጆቹ የመጨረሻው ወር የመጀመሪያ ሳምንት የቫሌንሺያ ማራቶን ይካሄዳል። ታዲያ በዚህ ሩጫ ላይ ድንቅ ብቃታቸውን በተለያዩ ውድድሮች ላይ ያሳዩ አትሌቶች እንደሚፋለሙ ከወዲሁ ተረጋግጧል። ይሁንና የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ በይበልጥ የሳበው የረጅም ርቀቶች ንጉሱ ቀነኒሳ በቀለ በዚህ ማራቶን መሳተፉ ነው። በርቀቱ ሶስተኛው የፈጣን ሰዓት ባለቤት የሆነው ኢትዮጵያዊው አትሌት በርካቶች ተስፋ እንደሚያደርጉት የማራቶንን ንግስና ከእጁ ሊያስገባ አሊያም የመጨረሻውን የኦሊምፒክ ተሳትፎውን ሊያሳካ የሚችልበት እድል እንደሚኖረው ይታመናል።

በመም፣ በሀገር አቋራጭ እንዲሁም በማራቶን ተደራራቢ ስኬቶችን ማጣጣም የቻለው አንጋፋው አትሌት የሰው ልጅ 42 ኪሎ ሜትርን ከ2ሰዓት በታች መግባት ይችላል የሚለውን እምነት ሊያሳኩ ከሚችሉ አትሌቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። እንደሚታወቀው በሁለት ኦሊምፒኮች እንዲሁም በአራት የዓለም ቻምፒዮና መድረኮች በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች 8የወርቅ፣ 1የብር እና 1 የነሃስ በጥቅሉ 10 ሜዳሊያዎችን ማጥለቅ የቻለ ጀግና አትሌት ነው። ከመም ባለፈም በሀገር አቋራጭ ውድድር በዓለም የእሱን ያህል በድል የተንቆጠቆጠ አትሌት አልታየም። ወደ ማራቶን ከተሸጋገረም በኋላ



በለንደን እና በርሊን ማራቶኖች ተደጋጋሚ ፉክክር በማድረግ በርቀቱ ክብረወሰኑን ለማሻሻል ከጫፍ ደርሶ እንደነበር አይዘነጋም። እአአ በ2019 በርሊን ማራቶን ላይ ያስመዘገበው 2:01:41 የሆነ ሰዓት በወቅቱ የዓለም ክብረወሰን ባለቤት ከነበረው ኬንያዊው አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ በ2 ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ነበር።

ይህ እንዲሁም ቀነኒሳ ካለው የሩጫ ብቃት አንጻርም በመም ውድድሮች ሁሌም አስከትሎት ይገባ ከነበረው ኪፕቾጌ እጅ ክብረወሰኑን ሊረከብ እንደሚችል የበርካቶች ግምት ነበር። በርግጥ የስፖርት ባለሙያዎች እንዲሁም ራሱ ቀነኒሳም በርቀቱ አዲስ ታሪክ የመጻፍ ችሎታ እንዳለው ሲያረጋግጡ ቆይተዋል። ይሁንና በተደጋጋሚ ጉዳት እየፈተነው መሆኑ በጉጉት ከሚጠበቅበት ውድድር ሳይቀር አቋርጦ ለመውጣት ሲገደድ ቆይቷል። በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የውድድር ዓመትም በቫሌንሺያ በሚካሄደው ማራቶን ላይ እንደሚካፈል ታውቋል። ይኸውም ሁሌም የአትሌቱን ድንቅ ብቃት ለመመልከት ለሚጓጉ የስፖርቱ ወዳጆች መልካም ዜና ነው።

ቀነኒሳ በዚህ ውድድር የሚካፈለውም ሁለት ዓላማዎችን ይዞ ሲሆን፤ የመጀመሪያው በሩጫ ሕይወቱ ተጨማሪውንና እጅግ ታሪካዊ ሊሆን የሚችለውን አዲስ ክብረወሰን ወደኢትዮጵያ ለመመለስ ነው። በቅርቡ በማራቶን ክብረወሰኑን የጠቀለለው ኬንያዊው አትሌት ኬልቪን ኪፕቱም በዚህ ውድድር ላይም ይሳተፋል በሚል ይጠበቃል። ይህም ፉክክሩን የሚያልቀው ሲሆን፤ ሰዓት ለማሻሻልም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ሌላኛው ደግሞ ወራት ብቻ ለሚቀሩት የፓሪስ ኦሊምፒክ ለራሱና ለሀገሩ ሶስተኛውንና ምናልባትም የመጨረሻውን ተሳትፎ ለማድረግ ነው። አትሌቱ ከዚህ ቀደም በማራቶን ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ ሀገሩን ለመወከል ተመርጦ ዝግጅት ሲያደርግ ቢቆይም በወቅቱ በነበረው ውዝግብ ምክንያት ከቡድኑ ጋር አለመጓዙ የሚታወስ ነው።

ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ የዚህ ውድድር ተሳትፎው ካለፈው ጊዜ ለየት የሚያደርገው ሌላኛው ጉዳይ ለሁለት አስርት ዓመታት ከቆየበት ማኔጅመንት ተለይቶ ከአዲስ የማኔጅመንት ጋር ውል በተፈራረመበት ማግስት መሆኑ ነው። ከዚህ ቀደም በርካታ ውጤታማ ኢትዮጵያዊያን እና ኬንያዊያን አትሌቶችን ባቀፈው ‹‹NN የሩጫ ቡድን›› ይሰለጥን የነበረው አትሌቱ ስፖንሰሩም ናይኪ የተሰኘው የስፖርት ትጥቅ አምራች ነበር። ያለፉትን ስኬቶች ያጣጣመውም በዚሁ ቡድን ውስጥ ነበር። አሁን ደግሞ የቻይና መሠረት ያለውና ‹‹ANTA›› ከተሰኘ ትጥቅ አምራች ጋር ለመሥራት ውል ያሰረ ሲሆን፤ የመጀመሪያውን ውድድር ከወር በኋላ ቫሌንሺ ላይ ያደርጋል።

ከቀድሞ ቡድኑ ጋር መለያየቱን ተከትሎም ‹‹ቀነኒሳ ስለቀጣዮቹ የሩጫ ዘመኖችህ መልካሙን ሁሉ እንመኛለን። ባለፉት ዓመታት ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን ሁሌም አብረንህ ነን›› ሲል ምርጥ አትሌቱን ሸኝቷል። አዲሱ ቡድኑና በግዝፈቱ ከናይኪ እና አዲዳስ ቀጥሎ የሚቀመጠው የትጥቅ አምራች ደግሞ ከቀነኒሳ ጋር መዋዋሉን ተከትሎም በማህበራዊ ድረገጹ ‹‹ቀነኒሳ ስለተቀላቀለን ተደስተናል። ከአትሌቱ ጋር በመሆንም አፍሪካ ላይ የስልጠና ማዕከል በመገንባት እንዲሁም በቀነኒሳ ሪዞርት ላይ አትሌቶችን የሚጠቅሙ ሥራዎች ላይ እናተኩራለን›› ሲል አስፍሯል። ይህም ስምምነቱ ከአትሌቱ ባለፈ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንንም ሊጠቅም የሚችል እንደሚሆን ይገመታል።